
# የአምባሳደር ሐዲስ ዓለማየሁ የሥርዓት ለውጥ ማስታወሻ

በክብር ዘበኛ ጦር ተሞክሮ የነበረው የመንግሥት ለውጥ እንደከሸፈ አቶ (አምባሳደር) ሐዲስ ዓለማየሁ ከውጭ አገር ወደ አዲስ አበባ መጥተው ንጉሡን «እንኳን ግርማዊነትዎንና ዙፋንዎን እግዚአብሔር አዳነ» ብለው ደስታቸውን ከገለጹ በኋላ ውይይት ቀጠለና አቶ ሐዲስ በአባሪ ቁጥር አንድ[29] የተያያዘውን የሥርዓት ለውጥ ማስታወሻ ለጃንሆይ አቀረቡ:: ጃንሆይ ማስታወሻውን ተቀብለው አለፍ አለፍ እያሉ ገለጥ እያደረጉ ዓይናቸውን ከመጨረሻው ገጽ ሲደርሱ ባዩት ነገር ቆጣ ብለው "እኛ ከንቱ ውዳሴ እንወዳለን? እንዲህ ብለህ ያቀረብከው? እኛ እኮ እናውቅሀለን" ብለው አቶ ሐዲስን ሲገስጿቸው፤ አቶ ሐዲስም ‹‹እኔም እኮ ዐውቀዎታለሁ:: ሊገድሉኝ፣ ሊያስሩኝ፣ ሊገርፉኝ እንደሚችሉ ዐውቃለሁ" ብለው እንደመለሱላቸው ንጉሡ በረድ ብለው ውይይቱ ቀጥሎ በጠቅላይ ሚኒስትሩ በአቶ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ሰብሳቢነት በጄኔራል ዐቢይና በአንድ ሌላ ሰው[30] ታይቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጡ::[31]



*አምባሳደር ሐዲስ ዓለማየሁ*

ጉዳዩን ተከታትለው ለማስፈፀም አቶ ሐዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተ ወልድንና ጄኔራል ዐቢይን ተመላልሰው አሳስበው በመጨረሻ ያገኙት መልስ ‹‹አሁን ያለውን የሥራ ውጥረት ታየዋለህ ቅድሚያ የሚሰጠውን ትተን ያንተን ማስታወሻ አናይም::›› የሚል ከአቶ አክሊሉ ሀብተ ወልድ፤ ‹‹አልኩ ለማለት ነው? ምንድነው እንዲህ የሚያጣድፍሕ›› የሚል ከጄኔራል ዓቢይ በመሆኑ ነገሩ ውጤት አልባ ሆኖ ቀረ::[32] አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ በማስታወሻቸው ያቀረቡት ሐሳብ ዋና ዋና ማተኮሪያ ፍሬ ነገር የሚከተሉት ናቸው::

---

[29] *አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ ለንጉሡ ያቀረቡትን ማስታወሻ አባሪ ቁጥር 1 ተመልከት፤*
[30] *አቶ ሐዲስ ከነግሩኝ ሦስተኛው ሰው ማን እንደሆነ ተዘንግቶኛል::*
[31] *አቶ ሐዲስ እንዳጫወቱኝ፣ አባሪ ቁጥር 1፤*
[32] *አቶ ሐዲስ እንዳጫወቱኝ፤*



*አምባሳደር ሐዲስ ዓለማየሁ*

የመፈንቅለ መንግሥቱ መነሳት ቅሬታ መኖሩን የሚያመለክት መሆኑን እንደ መግቢያ ይጠቅስና እንዲህ ዓይነቱን ችግር ለመቅረፍ የችግሩን ምንጭ ከስር ማጥራት እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባል። ከዚያም በሕዝብ መካከል ለቅርታና ለሁከት መነሻ ያሏቸውን ችግሮች ለመፍታት በቅንነት ያቀረቡትን ሐሳብ በስድስት ዋና ዋና ፍሬነገሮች ስር አስቀምጠዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ስሪት፡- ንጉሠ ነገሥቱ ከቀደሙት አስተዳደር የተሻለ ሥርዓት የዘረጉና በገዛ ፈቃዳቸው ሕገመንግሥት የሰጡ ቢሆንም ሕገመንግሥቱ የሚቀሩት ጉዳዮች መኖራቸውን ይጠቅሳል። እነርሱም የኢትዮጵያ ፓርላማ እንደሌሎች አገሮች ፓርላማ የመወሰን ሥልጣን የሌለው መሆኑ፣ የመንግሥት ባለሥልጣናት በንጉሡ ፈቃድ የሚሾሙ እንደመሆናቸው ለጥፋታቸው ተጠያቂ የሚሆኑበት ሥርዓት የሌለው መሆኑ፣ የመጨረሻው ሥልጣን የሚመነጨው ከሕዝብ አለመሆኑና የመሳሰሉት ችግሮች ቅርታ የፈጠሩ መሆኑን ያለክታል።

የኢትዮጵያ መንግሥት አስተዳደር፡- የመንግሥት ሠራተኞች አገልግሎትና ችሎታን የሚመዝን ደሞዝና ደረጃን ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት የሌለው በመሆኑ ሥራዎች የሚሠሩት በጉቦና በዘመድ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ትንንሹ ነገር ሳይቀር ያለንጉሡ ፈቃድ የማይፈፀም መሆኑ ሁሉ አገልግሎትን በአግባቡ ለመስጠት እንዳይቻል በማድረጉ የፈጠረው ቅርታም አለ።

የኢትዮጵያ ልማት፡- የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚባለው በውስጧ የሚኖሩትን ትግሬ፣ አማራ፣ ኦሮሞና ሌሎችም ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ማኅበረሰቦች አንድ ላይ ቢሆኑም፤ በብዙ ጉዳዮች የሚያስተሳሥራቸው የኅብረት ማሠሪያ ያላቸው ናቸው ለማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም ከእነርሱ ውስጥ አንዳንዶቹ ከተቀሩት የበላይነት የሚሰማቸው፣ ሌሎቹ ባንበልጥ አናንስም የሚሉና ይሔንን ለማረጋገጥ አጋጣሚ የሚጠብቁ፤ የተቀሩትም የበታችነት የሚሰማቸውና የበላይ ነን ከሚሉት ክፍሎች ኃይል ሰብሮ ነፃ የሚያወጣቸው ክፉ ቀን እንዲመጣላቸው የሚጠብቁና የሚመኙ በመሆናቸው፤ አንድነታቸው ከመንግሥት ጦር ኃይል ውጪ በስም ብቻ ነው ለማለት የሚያስደፍር ነው። በኢኮኖሚም አገሪቱ ያለችበት ሁኔታ ከአፍሪካ አገሮች አንፃር እንኳን ዝቅ ያለ መሆኑ በትምህርት አቅርቦትም ዝቅተኛ መሆኑና የመሳሰሉት ሁሉ ባለሥልጣናት ጥቅማቸውን ለማሳደድ በመሞከራቸው ነው እየተባለ መነቀፉም ሌላው የቅርታ ምንጭ ነው።

የተጠራቀመ ዕዳ፡- ካለፉት አስተዳደሮች የተላለፉ ያልተፈቱ ችግሮች የፈጠሩት ጫናም በዘመኑ ያለው ባለሥልጣን ቢሠራም ምስጋና እንዳያገኝ ማድረጉና በሰው ባህሪይ ውስጥ ያለና የተለመደ መሆኑ ያለመርካት ሁኔታም ነገሩን አባብሶታል።

የሐሳብ መግለጽ መብት፡- ምንም እንኳን ሐሳብን የመግለጽ መብት በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተካተተ ቢሆንም የመንግሥትን ጉድለት ለመግለጽ በጋዜጣ መጻፍም ሆነ በጉባኤ መናገር አይቻልም ተብሎ መታመኑ በያካባቢውና በየጓዳው

መንቀፍና ማማቱ እንዲበዛ አድርጓል። የሐሜቱ መሠረት ሃሰት መሆኑን መንግሥት በቃልም ይሑን በሥራ ማስረዳት ፈንታው ነው። እስከዛው ግን የታፈነው ካልተነፈሰ ወደመፈንዳት ሊደርስ ይችላል።


ሰላምን ለመሥራት የሁከት መሠረት ማጥፋት ያስፈልጋል፡- ደስታ ለማጣት፣ ለቅርታና ለሁከት ምክንያት የሆኑ ነገሮች መፍትሔ ሳያገኙ ዘላቂ የሆነ ሰላም ሊገኝ እንደማይችል፤ የመንግሥት ሥሪት ወደፊት መሻሻሉ የማይቀር እንደመሆኑ ንጉሡ መሻሻሉን በራሳቸው ቢያደርጉ በታሪክ መልካም ሥፍራ ስለሚኖራቸው አባት የደረሰ ልጁን በራሱ ፈቃድ እንዲኖር እንደሚፈቅድለት የኢትዮጵያ ሕዝብ እየጎለመሰ በመምጣቱም ራሱን እንደቻለ ሕዝብ እንዲያስቡ ያመለክታል።

በመጨረሻም የሐሳብ ማጠቃለያ በሚል ንዑስ ርዕስ ስር የተጠቀሱትን ችግሮች ለመፍታት ሕገመንግሥቱን ማሻሻል፣ የመንግሥቱን አስተዳደር ማስተካከል፣ ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት በዓመትና ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ ተግባር ላይ እንዲውል ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይመክራል። የሚደረገው የመንግሥት አስተዳር ማሻሻል እርምጃ ሐሳብ ሁከት አስነሥተው የነበሩ ሰዎች[33] ያነሱት ስለነበረ መንግሥት በእነርሱ ተመርቶ ነው መባሉን ጠልቶ እርምጃውን ለማዘግየት መሞከር እንደሌለበትም ያስጠነቅቃል። በማስታወሻው የተነሱ ነገሮችና ቋንቋቸው መረር ያለ ቢሆንም እውነቱ ከተራ ሙገሣ የሚበልጥ ስለሆነ ብቻ እንደሆነ በትህትና በመግለጽ ማስታወሻውን ያጠናቅቃሉ።

[33] የታኅሣሡን ግርግር ለማለት ነው።

## የአምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ ማስታወሻ[34]

ከተመደቡበት የሥራ ኃላፊነታቸው ባለፈ ለጃንሆይ ቀራቢ ታማኝና ልዩ አማካሪ በመሆን ለአስተዳደሩ ይጠቅማል የሚሉትን ምክር ሲያቀርቡ የነበሩት አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄም በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም. ለንጉሡ ማስታወሻ ልከዋል፡፡ በዚህ ማስታወሻቸው ሃገር ውስጥ ባለው ማኅበረ ፖለቲካ ችግር መባባስ ምክንያት ወደሃገር መመለስ እንደቸገራቸው፣ ሁኔታውን ማስተካከል ካልተቻለ ወደብጥብጥ እንደሚያመራ፣ ይሔን አስተያየታቸውን የሰጡት በኢትዮጵያዊነት መብታቸው መሆኑን፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዙፋኑ የሰጠው ልባዊ አክብሮት ዘላቂ ሆኖ በታሪክ ቅርስነት እንዲጠበቅ በመንግሥቱ በኩል የታሰበበት አለመሆኑ፣ መለኮታዊ መብት የተባለው ቲዎሪ የተሳሳተ መሆኑን ቢረዳውም ሕዝቡ ዘውዱን ታሪካዊ ሲምቦል ወይም ምሳሌ አድርጎ በክብር ሊያኖረው የፈቀደ ብቻ መሆኑን፣ ጣኦታዊ ስግደት እንዲያደርግ ማስገደድ ዘውዱን ለማስረገጥ ካልሆነ በቀር አለመጥቀሙን፣ እየተደጋገመ ሕዝቡ ኃላፊነትን ለመቀበል አልደረሰም መባሉም ስህተት መሆኑን እና ይህን ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ለማሻሻል የሚቻለው ጃንሆይ ዘውዱን ለራሳቸው አስቀርተው አስተዳደሩን ለሕዝብ በመስጠትና የዲሞክራሲ መንፈስ በማስገባት እንደሆነ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡




*አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ*

አምባሳደር ብርሃኑ ይህን ማስታወሻ በመጻፋቸው ንጉሡ ተቀይመው የእሳቸውን ሕይወት ለማስጠፋት በሺ የሚቆጠር ገንዘብ ከሚወጣም ለድሆች ቢውል እንደሚሻል፣ ይህንን ሐሳብ እሳቸው የሰጡትም ሪቮሌሽን እንዲነሳና የማንም ደም እንዲፈስ ፈቅደው አለመሆኑን በመግለጽ ስጋታቸውን ያመለክታሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ማስታወሻው በኢትዮጵያ ወጣቱ ሽማግሌው ሴቱ ወንዱ የአኗኗር ዘዴ ውሉ ቢዘበራረቅበትም አምላካችን ፈጣሪያችን እያለ የሚደልላቸው በጭንቀት እንደሆነ ያለው ሕገ መንግሥት ዲሞክራሲ ለማስገባት የሚረዳ ካለመሆኑም በላይ ያንኑም አክብሮ ለመጠበቅ በአንቀጽ ፳፩ እንደተመለከተው ከንጉሠ ነገሥቱ በመሀላ የተሰጠው ቃል ፈርሷል እያሉ አያሌ ኢትዮጵያውያን እንደሚያማርሩ፣ ንጉሠ ነገሥቱ በበኩሉ መሀላውን የሚጠብቅ ካልሆነ ሕዝቡም በመሃላው ታስሮ እንደማይኖር በልጅ ኢያሱ ጊዜ የደረሰው ሁኔታ ምሳሌ ሊሆን እንደሚችል የሚያስጠነቅቅ ነው፡፡

---

[34] አባሪ ቁጥር ሁለት



*አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ*

## የአምስቱ የመንግሥት ከፍተኛ ባላሥልጣናት[35] የመንግሥት ሥርዓት ለውጥ ጥያቄ ማስታወሻ



ልዑል ራስ አሥራተ ካሣ




ሌ/ጄኔራል ዐቢይ አበበ



ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻ



ኮሎኔል ታምራት ይገዙ



ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት


በክብር ዘበኛ ጦር ተሞክሮ የነበረውን የመንግሥት ለውጥ ለማክሸፍ በዋናነት ተሰልፈው ከነበሩት መሪዎችም ንጉሥ ነገሥቱ የአስተዳደራቸውን ሥርዓት እንዲያሻሽሉ ጠይቀዋል። እነርሱም ጄኔራል መርዕድ መንገሻ (የመከላከያ ሚኒስትር)፣ ልዑል ራስ አሥራተ ካሣ (የኤርትራ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እንደራሴ)፣ ጄኔራል ዐቢይ አበበ (የሕግ መወሰኛ

[35] አባሪ ሦስት

# የአምስቱ የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት[35]
# የመንግሥት ሥርዓት ለውጥ ጥያቄ ማስታወሻ




ልዑል ራስ አሥራተ ካሣ



ሌ/ጄኔራል ዐቢይ አበበ



ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻ



ኮሎኔል ታምራት ይገዙ



ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት

በክብር ዘበኛ ጦር ተሞክሮ የነበረውን የመንግሥት ለውጥ ለማክሸፍ በዋናነት ተሰልፈው ከነበሩት መሪዎችም ንጉሥ ነገሥቱ የአስተዳደራቸውን ሥርዓት እንዲያሻሽሉ ጠይቀዋል፡፡ እነርሱም ጄኔራል መርዕድ መንገሻ (የመከላከያ ሚኒስትር)፣ ልዑል ራስ አሥራተ ካሣ (የኤርትራ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እንደራሴ)፣ ጄኔራል ዐቢይ አበበ (የሕግ መወሰኛ

[35] አባሪ ሦስት

ም/ቤት ኘሬዝዳንት)፣ ኮሎኔል ታምራት ይገዙ (የከፋ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ) እና ብላታ (በኋላ ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት- የማስታወቅያ ሚኒስትር) ናቸው። አምስቱ ባለሥልጣናት አንድ ላይ ሆነው ሁለት ቀንና ሌሊት ሳይለያዩ የጻፉትን ፲፰ ገጽ አስቸኳይ የመንግሥት ሥርዓት ለውጥ ይደረግ የሚል የምክር ሐሳብ አንድ ላይ ሆነው ለንጉሠ ነገሥቱ አቀረቡ።[36]

ጃንሆይ ግን የመንግሥት የሥርዓት ለውጥ ሐሳብ ከማንም ይምጣ ከማን መስማትም ሆነ መቀበል የማይፈልጉ ሆኑ። ሁሉንም ጠረጠሩ። የሚያምኑት አጡ። እንዲህ በመሆኑ እነዚህ ቅርብና ታማኝ የነበሩ ከፍተኛ ባለሥልጣኖችን ጭምር ካለማመናቸውም በላይ ለወደፊቱም እየተገናኙ ቀጣይ ነገር ከማሰብና ከመሥራት አይመለሱም ብለው ጠረጠሩ። ከዚያም አልፈው ወደ ነውጥ ይሸጋገራሉ ብለው ሰጉ። ማስታወሻውን በተቀበሉበት ምሽት የሹም ሽር አዋጅ አድርገው አምስቱም በቅርብ እንዳይገናኙ በሹመት ከአዲስ አበባ ከተማ አወጧቸው። አምስቱ ባለሥልጣኖች ያቀረቡት ማስታወሻ በአባሪነት የተያያዘ ቢሆንም ከዚህ እንደሚከተለው ድርሞውን አቀርባለሁ።

አቅራቢዎች ማስታወሻውን ለንጉሠ ነገሥቱ ለማቅረብ የተገፋፉበት ምክንያት "ለግርማዊነትዎ ያለን የታማኝነት መንፈስና ከፍ ያለ አፍቅሮት ስሜት ሲሆን ስለመንግሥቱ መፅናትና ስለአገራቱም ልማት በማሰብ በመቆርቆር" ነው ሲሉ ገልጸዋል። እውነትም አመልካቾቹ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን የተወለዱ በደረጃና በሹመት ያደጉ በመሆናቸው በላቸው ወገናዊነትና ተቆርቋሪነት ሲሆን፤ የአመልካቾቹ አባቶች ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አብረው የደከሙና የሚያገለግሉ የንጉሠ ነገሥቱም ደጋፊዎች ሆነው የተሰለፉ መሆናቸው ይታወቃል።

ንጉሡንም ኢትዮጵያና ሕዝቧን ወደ ከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ ለማድረስ ግባቸው አድርገው በመነሣት ለአለፉት ፴፫ ዓመታት ያደረጉት ድካም አገሪቱን ከፍ ወዳለ ደረጃ ማድረሳቸውን፣ ከዚህ ጥረት ጋር ተያይዘው የተፈጠሩት ችግሮች መኖራቸው በእርግጥ እየታየ መምጣቱንና የነዚህን ችግሮችም መፍትሔ ማስገኘት ከማንኛውም ጉዳይ ቀዳሚነት የሚሰጠው መሆኑንና ለመፍትሔውም ቅን ያገልጋይነት ፈቃደኝነት እንዳለ ያረጋግጣሉ።

በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. መፈንቅለ መንግሥት መሞከሩን ያስታውሱና ምንም እንኳ ንጉሠ ነገሥቱ በየጊዜው ያጋጠሙ ችግሮችን በየደረጃው እየፈቱ ቢሆንም፤ በተመሣሣይ ችግር የሚያልፉ መሪዎች ቆራጥ የመፍትሔ እርምጃ በመውሰድ በታሪክ ታላቅነታቸውን እንደሚያስመሰክሩት ሁሉ ንጉሠ ነገሥቱ ጊዜን በመሽቀዳደም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ያለባቸው መሆኑን በታማኝነት ይገልጻሉ። ዘመናዊ ትምህርት

[36] አምስቱም ከፍተኛ ባለሥልጣናት ለግርማዊ ጃንሆይ አቅርበውት የነበረው ማስታወሻ በአባሪነት ተያይዟል።

እንዲስፋፋ በመደረጉ ዘመናዊ አስተሳሰብ ሲጎለምስ በአንፃሩ ነባርና ልምዳዊ አስተሳሰብም ተቀናጅቶ እንዲሄድ ሚዛን የጠበቀ አመራር መኖሩ የሚደነቅ ቢሆንም፤ የጠላት ወረራ ያመጣው ለውጥ በገሀድ አስተሳሰብ ላይ ሲታከል የቆየው ሚዛናዊነት እየቀነሰ እንዲሔድ አድርጓል።

አዲሱ የባሕል ተፅዕኖ ያስከተለውን የሶሺያል፣ የፖለቲካ፣ የኢኰኖሚና የግል ችግር አለመፍታት የመንግሥትን ብቃት ጥርጣሬ ላይ ከመጣሉም በላይ ችግሩን እንፈታለን ባዮች መንግሥት ለመገልበጥ መሞከራቸው የችግሩን ደረጃ እንደሚያሳይ፤ የመገልበጥ ጥንስስና ሙከራ ተደጋግሞ ሲደረግ ዐድማው ቢከሽፍም የዐድማው መንስኤዎች በአገሪቱ እንዳዣበቡ መገኘታቸው፣ ቀን ሲገፋ ትውልድ እየጨመረ ሲሔድ የጐሉት ችግሮች ካለመፈታታቸው ሌላ በተደራቢነት የሚመጡ አዲስ ችግሮች መደራረብ ውስብስብነት ስለሚፈጠር በአጣዳፊ ለመፍታት የሚደረገው ጥረት ቆራጥነትን የሚጠይቅ መሆኑንና ከማመልከት በላይ መፈታት ያለባቸው ችግሮችንም ለይተው አስቀምጠዋል። እነርሱም የአስተዳደር ጉዳዮች፣ የኢኰኖሚና የሶሻል ጉዳዮችና የፖለቲካና የሞራል ጉዳዮች ናቸው።

**የአስተዳደር ጉዳዮች፡-** በንጉሠ ነገሥቱ በልምድ የቆየው የብዙ ሺህ ዘመናት የአስተዳደር ኋላቀርነት በሕገ መንግሥት እንዲመራ ቢደረግም፤ የዘመኑ እድገት የበለጠ መሻሻልን እየጠየቀ በመምጣቱ ሕገ መንግሥቱ መሻሻል ብቻ ሳይሆን ዲሞክራሲን ማስፈን ግድ ማድረጉን ይጠቁማል። ምክንያቱም ዲሞክራሲ ከሌለ ችግሩ እየተባባሰ የሚቀጥል ይሆናል። መሻሻል ካለባቸው አንቀፆችም መካከል፡- በንጉሠ ነገሥቱና በሥራ አስኪያጆች መካከል ያለው ሥልጣንና ኃላፊነት መወሰን፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከሐሜትና ከአስተዳደር በላይ ሊሆን የሚገባውና ከውስጥ ችግርና ከውጭ ጥቃት ለመዳን በበላይነት መምራት ጠቀሜታው የላቀ ስለመሆኑ፣ ሕገ መንግሥቱ ከሕዝቡ ፍላጐትና እርምጃ ጋር እየተመዛዘነ ካልሔደ አለመረጋጋትና የአደጋ ሥጋት የሚቀጥል መሆኑ፤ የመሻሻሉ አስፈላጊነት የንጉሠ ነገሥቱን የበላይ ኃላፊነት እና ጠቅላላ ሥልጣን ለመቀነስ ሳይሆን ፓርላማውና ሚኒስትሮች የተጣለባቸውን አደራ በትክክለ መወጣታቸውን ለመቆጣጠር እንዲቻል መሆኑ፤ ይህ ባለመደረጉ ሚኒስትሮች ከሕዝብ ወቀሳ ለመዳን ግርማዊነትዎን በማሳጣት ከሕዝብ እንዲፈራቀቁ ከማድረጉም በላይ የድርሻውን ሥራ በትጋት ለመወጣት ማመካኛ ከመሆኑም ሌላ ለግል ጥቅም ከማጭበርበር አልፎ ከመንግሥት የሚጠበቀውን ከፍተኛ ዐላማ በዚህ የተነሳም ሕዝብ በመንግሥት ላይ ያለው ዕምነት እንዲቀንስ የሚያደርግ ሲሆን፤ በአንፃሩ ተስፋ የቆረጡ ተቃዋሚውን ስለሚደግፉ ተቃዋሚውን ቡድን ያጠነክራል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጓደኞቹንና የቅርብ ሰዎቹን መርጦ በማቅረብ የሚያደርገው ሹመትና ፖሊሲዎቹን እንደተመቸው አዘጋጅቶ ለፓርላማና ለዘውድ ምክር ቤት በማቅረብ የሚያፀድቅበት ሒደት አግባብ ስላልሆነ መወገድ አለበት። የፓርላማ አባላት ለመመረጥ የሚያስችላቸው የብቃት መመዘኛ ወጥቶ በውድድር ተመርጠው እስካልሠሩ ድረስ የሕዝብና የመንግሥትን ጥቅም የሚያስጠብቁ አለመሆናቸው መቀየር አለበት። ይህ ሁኔታ እስኪመቻችና ፓርላማው እስኪደራጅ አንድ የመንግሥት

ምክር ቤት በአስቸኳይ ተሰይሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩንና ቡድኑን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥልጣን ቢሰጠው አስፈላጊና ጠቃሚ መሆኑ፤ ይህ ካልተደረገ በዘልማድና በዘፈቀደ የሚመሩ መንግሥታት በተለይ ከኢትዮጵያ አጎራባች አገሮች የሚነዛ አሉባልታ ለባሰ ችግር የሚዳርግ አስጊ ሁኔታን እሊፈጥር እንደሚችል ያሳስባል።

የኢኮኖሚና የሰሻል ችግሮች፦ ሁለቱም የኑሮን ችግሮች የሚመለከቱ ከአስተዳደር ጋር የተያያዙ ናቸው። የሕዝቡ የኑሮ ፍላጎት የሚሞላው በኢኮኖሚ ዕድገት ነው። ኢኮኖሚ የሚያድገው ደግሞ በሥራ ነው። ሥራ ሊሥፋፋ የሚችለው ደግሞ በመንግሥት ነው። ይህን ለማስፋፋት ደግሞ የቢሮክራሲ ትብትብ እየተቃለለ መሔድ አለበት። በአስተዳደር፣ በዳኝነት ነው። በፀጥታና በንብረት ይዞታ ያለው ጉዳይ ሁሉ በአስቸኳይ መፍታት ግድ ነው። ድህነትና ችግር ሲበዛ በሕዝቡ በተለይ በወጣቱ ላይ ብስጭትና ተስፋ መቁረጥ በማሳደር ወደጥፋት የሚያመራና የሚገፋፋ ይሆናል። ትዳር ባላቸውና በሌላቸው መካከል መለያየት፣ ሀብት ባላቸውና በሌላቸው መካከል የምቀኝነትና የመለያየት መንፈስ ይፈጠራል። በሞራል ረገድም እምነት እየጐደለ፣ ሌብነትና ሽፍጥ ማታለል እየሰፋ ሲሔድ ኮራፕሽኑ ሲበዛ በባዕድ ገንዘብ እስከመገዛት ብሎም አገርን እስከመሸጥ ያደርሳል።

ፖለቲካና ሞራል፦ ፖለቲካ፣ ሞራልና አስተዳደር ከኢኮኖሚ ጋር በጣምራ የሚራመዱ ናቸው። በአዲሱ ትውልድ ላይ የሚደርሰው የሞራል መመሰቃቀል እና ልዩ ስሜት በተራው ሕዝብ መካከል ሳይቀር የተሰራጨው ስብከት የቆየውን ችግር የሚያባብስ ነው። ችግሩን የሚያባብሰው የኢኮኖሚው ሁኔታ በመሆኑ ሥራ መስፋፋት አለበት። ወጣቱ ሥራና ትዳር እንዲይዝ መንግሥት ሥልት ካልቀየሰ፤ የተመኘውን ባለማግኘቱ እዳር ሆኖ በማሽሟጠጥና ችግር ፈጣሪ አቃቂር በማውጣት ሕዝብና መንግሥትን ያፋልጣል። ከወጣቱ ቀጥሎ አሣሳቢው ክፍል ወታደሩ ነው። ወታደሩ የራሱ የሆነ ድርጅት ያለው የመንግሥት አካል ቢሆንም፤ በመንግሥት ውስጥ የመንግሥት ያህል ነው። በመሆኑም በፖለቲካ መሣሪያነቱ ብዙ ሀገሮች ሲጠቀሙበት ይታያል። በሃገራችን ሕዝቡ የወታደርነት ባህል ያለውና ባለመሣሪያ በመሆኑ ሥልጣን ለመያዝ ያዳግተዋል፤ ሆኖም የማለስለሻ ዘዴ በመፍጠር መንግሥትን በኃይል ገልብጦ ሥልጣን ሊይዝ ስለሚችል ያለው አሳሳቢነት ግልጽ ነው። ይህን ለመቀነስ ሕዝቡ በመንግሥት እንዲያምን በማድረግና ሚዛኑን በማስተካከል የሕዝብ መከላከያ መፍጠር ተገቢ ነው።

የሕዝብን አመኔታ ለማግኘት የሚቻለው በአስተዳደርና በዳኝነት ሲደሰት በመሆኑ ለዚህም ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው አገረ ገዢዎች በመሆናቸው ለዚህ ቦታ የሚታጩ ሰዎች ባላቸው የሥራ ልምድ በሕዝብ ተወዳጅነት ተመርጠው የሕዝብን አክብሮት ያገኙ መሆን አለባቸው። እነሱም ከመንግሥት የቢሮክራሲ ትብትብ ውጪ ነፃ ሆነው እንዲሠሩ መደረግ አለበት። በጠቅላይ ግዛቶች የሚነሱ ተቃውሞዎች ቢኖሩ ከማዕከል ድጋፍ በማግኘት ብቻቸውን ሊቋቋሙና ሊያስወግዱት ይችላሉ። ከወጣቱ የበሰሉትን በመምረጥ የመንግሥት ኃላፊነት በመስጠት የመንግሥት ወገን ማድረግ፣ የጐሣ ልዩነትን ለማዳከም አገረ - ገዥዎችን በትውልድ አገራቸውን በተወላጅነትና በመሣፍንትነት በሚጠሩበት አውራጃ መሾም በችግር ግዜ በመንግሥት ጐን

እንዲሰለፉ ያደርጋል። የአገሪቱን አንድነት ለማጠናከር ከተሞች እንዲበዙ ሠፊ መሬቶች እንዲለሙ እርሻና ከብት ርቢ እንዲለማ እንዲስፋፋ ማድረግ ያስፈልጋል።

**ስለውጭ ፖለቲካ** :- በምሥራቅና በምዕራብ መካከል ያለው የፖለቲካ ልዩነት ሕዝቦችን በመሣሪያነት ሊያበጣብጥ ስለሚችል የአገራችን የውጭ የፖለቲካ ግንኙነትን በጥንቃቄ መያዙ ችግሩን ከማርገብ አልፎ ጥቅም ማስጠበቂያ ሊሆን ይችላል። ኢትዮጵያ ሁለቱን አይዲዮሎጂዎች በኒውትራሊቲ (በገለልተኝነት) የጠበቀች ቢሆንም፣ ሥጋቱ ለጊዜው ይወገድ እንጅ አሁንም ጥንቃቄን ይጠይቃል። በተለይ ትኩረትን የሚጠይቀው አስጊ ሁኔታ ግን የሃይማኖትና የዘርን ልዩነት በመሣሪያነት የሚገፋፉ የዐረቦችና የእስላሞች ፖለቲካ ነው። ይህን ተቋቁሞ የቆየው የሕዝቧ የሃይማኖት ፅናትና የሞራል ብርታት በመሆኑ አሁንም ሊበረታታ ይገባል።

ባጠቃላይ እነዚህ በማስታወሻው የተጠቀሱ ጉዳዮች ጥልቅና ሠፊ ጥናት የሚጠይቁ ቢሆንም አቅራቢዎቹ ከወዲሁ የችግሩን አስቸኳይነት በመገንዘብ ለእርምጃ አወሳሰድ እንዲረዳ መሆኑ አመልክተዋል። በዚህ መሠረት የጠቁቆሟቸው መፍትሔዎችም

፩ ሕገ - መንግሥቱ እንዲሻሻል
፪ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥራ ቡድኑን መርጦ የሚያቋቁመው የሚኒስትሮች ካቢኔ በፓርላማ ወይም በመንግሥት ምክር ቤት ወይም በዘውድ ምክር ቤት ፊት የሥራ ፕሮግራሙን አቅርቦ እንዲያስረዳና በድምፅ ብልጫ ሲደገፍ ብቻ እንዲሠራበት፣
፫ ፓርላማው ወይም የመንግሥት ምክር ቤት ወይም የዘውድ ምክር ቤት በመንግሥት ሥራ ላይ ሙሉ የመቆጣጠር ሥልጣን እንዲኖረውና ሲደገፍ እንዲቀጥል ሲነቀፍ እንዲሰናበት እንዲደረግ፣
፬ የፓርላማ ተወዳዳሪዎች መመዘኛ ጥብቅ እንዲሆን፣
፭ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠሪነቱ ለንጉሠ ነገሥቱ መሆኑ ቀርቶ በርዕሰ መንግሥቱ ለሚሾመው ምክር ቤት እንዲሆን፣
፮ የሚኒስትሮች ተጠሪነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካይነት ለፓርላማው በንጉሠ ነገሥቱ ለሚሾመው ምክር ቤትም እንዲሆንና
፯ የጠቅላይ ገዥዎች ሥልጣን እንዲስፋፋና አዲስ ደንብም እንዲወጣላቸው እንዲደረግ የሚሉ ናቸው።


እንደመደምደሚያም በንጉሠ ነገሥቱ ያለመታከት ጥረት ኢትዮጵያ እደረሰችበት የዕድገት ደረጃ ብትቆናጠጥም የገጠማትን ችግር የማስወገድ ጥረት ካልተፋጠነ በአመልካቾቹና አልፎም በልጆቻቸው ጊዜ ችግር የሚያስከትል ከመሆኑም በላይ ንጉሠ-ነገሥቱ ለአመልካቾች የሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የማይበቁ መሆናቸውን መስክረዋል። በአጠቃላይ የሀገሪቱ ችግር ሣይፈታ ቀርቶ የንጉሠ ነገሥቱ የአመልካቾች አባቶች ድካምን ከንቱ የሚያስቀርና በተተኪው ትውልድ የሚያስወቅስ ታሪክንም የሚያጉድፍ ስለሚሆን በንጉሠ ነገሥቱ አመራር ሀገሪቱ ከጥፋት እንድትድን እንዲሞከር አጥብቀው ተማጥነው ይህ በቅንነት የቀረበ ሐሳብ ተግባራዊ ሳይሆን ቢቀር የሚያስከትለው ችግር የማይገፋ እንደሚሆን ገልጸዋል።

# የጄኔራል ዐቢይ አበበ የእንታረም ምክር



ሌ/ጄኔራል ዐቢይ አበበ

የአምስቱ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት የመንግሥት የሥርዓት ለውጥ በአስቸኳይ እንዲደረግ የቀረበው ማስታወሻ ውጤት ባለማስገኘቱ ከአምሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች አንዱ ጄኔራል ዐቢይ አበበ እንደገና የመንግሥቱ ሥርዓት በነበረው ሁኔታ ቢቀጥል በመንግሥትና በበደል ፈፃሚዎቹ ላይ ከፍ ያለ ችግር የሚያስከትል ስለሆነ ከአሁኑ ዐውቀው እንዲታረሙ ሐሳቡን በሕዝብ አእምሮ ለማስረጽ መጽሐፍ ጽፈው ለማሠራጨት አሰቡ።

ጄኔራሉ የንጉሠ ነገሥቱ ቀራቢና ከፍተኛ ባለሥልጣን ሆነው ሳለ ሀብት ለማግበስበስና ካልተቀዳደሙና በግለሰብ ጉዳይ ገብተው በሕዝብ ላይ በደል ካላደረሱ በጣት ከሚቆጠሩ የዐጼ ኃይለ ሥላሴ ከፍተኛ ባለሥልጣን አንዱ ነበሩ። እንደውም በጉናቸው የነበሩ የመንግሥት ባለሥልጣኖች የሚያደርሱት የአስተዳደር በደል እና የሀብት ማግበስበስ ጉጉት ያሳሰባቸውና ያስጨንቃቸው ነበር። ስለዚህ *"አውቀን እንታረም"* የተባለ አጥፊዎች ከስህተታቸው እንዲታቀቡ ለመምከር እና ለማስጠንቀቅ ያለመ መጽሐፉ ጻፉ። ጄኔራል ዐቢይ አበበ በኤርትራ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እንደራሴ ስለነበሩ መጽሐፉን አሥመራ አሳተሙ። መጽሐፉን በአዲስ አበባ አሳትሞ ለማሰራጨት ግን መጀመሪያ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ሣንሱር ክፍል ተልኮ የሣንሱር ክፍሉ የመንግሥትን ፖለቲካ ወይም የሕዝብን ስነ ልቡና የሚጐንጥ ነገር እንደሌለበት ማረጋገጫ ያስፈልገው ስለ ነበር፤ በደንቡ መሠረት በወቅቱ የማስታወቂያ ሚኒስትር የነበሩት ብላታ ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት ይቀርብላቸዋል። ብላታ ግርማም የመጽሐፉን ረቂቅ አንብበው "ይህ መጸሐፍ ሕዝብ እጅ ቢገባ ችግር ያመጣል›› የሚል አስተያየታቸውን ሰጥተው ደራሲው እንዳይቀየሟቸው በማሰብ ረቂቁን ይመልሱታል። ንጉሠ ነገሥቱም የብላታን አስተያየት አንብበው ትእዛዝ አዘል ምክር ለጄኔራል ዐቢይ ሰጥተዋል። ሁኔታውን በቅጡ ለመረዳት እንዲያስችለን በጀኔራል ዐቢይ፣ ደጃዝማች ግርማቸውና በንጉሠ ነገሥቱ መካከል የነበረውን ምልልስ የሚያሳዩ ሦስት ሰነዶች ከዚህ በታች ቀርበዋል።



ሌ/ጄኔራል ዐቢይ አበበ



የሌፍተናንት ጀኔራል ዐቢይ አበበን «አውቀን እንታረም» መጽሐፍ ለማገድ የደጃዝማች ግርማቸው የመጀመሪያው ደብዳቤ

ቀ.ኃ.ሥ.ላ.

ለሊ.የተና.ጀኔራል ዐቢይ፡ አ።


ጤናህን፡ እንደምን፡ ነህ፡

እኛ፡ ሥላሴ፡ ይመስገን፡ ደህና፡ ነን።

ጊዜ፡ በማግኘት፡ የጻፍከውን፡ መጽሐፍ፡ ተመለከትነው። ለብላታ፡ ግርማቸው፡ ልኬለታለሁ፡ ስላልከው፡ በሱም፡ በኩል፡ ምን፡ አሳብ፡ እንዳለው፡ አስረድቶናል።

አንተ፡ የጻፍከው፡ በንጹሕ፡ ልቡና፡ ባለሥልጣኖችንና፡ ሕዝቡንም፡ ለመምከር፤ ለማረም፤ ለማስጠንቀቅም፡ እንደሆነ፡ በኛ፡ በኩል፡ የተረዳነው፡ ቢሆንም፡ በውስጥም፡ ሆነ፡ በውጭ፡ ያሉ፡ ተቃዋሚዎች፡ ክፍሎች፡ ለመገፋፊያና፡ ለመበረታቻ፡ እንዳ ይጠቀሙበት፡ ከጊዜው፡ ጋር፡ አስተያይተህና፡ አመዛዝነህ፡ ጠቃሚ፡ በሚመስልህ፡ እኳኋን፡ አቃንተህ፡ ብትልከልን፡ እንዲገና፡ እንዲታ ተም፡ አስፈላጊው፡ ይደረጋል። ነሐሴ፡ ፳፯ ቀን፡ ፲፱፻፶፫ ዓ.ም.

ጃንሆይ ለሌ/ጄኔራል ዐቢይ በክፉል በራሳቸው የእጅ ጽሑፍ የጻፉት ደብዳቤ


ኅዳር 30/1955 ዓ.ም.

ደጃዝማቾች ግርማቸው ለሌ/ጄኔራል ዐቢይ በድጋሚ የጻፉት ደብዳቤ

## ያንዣበበውን ችግር ለመፍታት ታስበው ከነበሩ ሙከራዎች[37]

ማስታወሻቸውን ለንጉሡ የላኩት ሰዎች ሐሳብና ሌሎችም እንቅስቃሴዎች አልተሳኩም፤ ችግሩም አልተቀረፈም። ለወደፊትም የታሰበ ነገርም አልነበረም። የመንግሥቱ አስተዳደር ተስፋ የሚሰጥ አልሆን እያለ መሔዱ ግን ግልጽ እየሆነ ሔደ። እንዲህ ችግሩ እየተባባሰ ሲሔድ ከየአቅጣጫው አንዳንድ ሐሳብ በግልጽም ባይሆን መነሳቱ አልቀረም። በኋላም አንዳንድ ዕለታዊ ችግሮችን ለመፍታት ሙከራ ይደረግ ነበር። ከሙከራዎቹ እኔ ለማወቅ የቻልኩትን እጠቁማለሁ በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. እኔ ጎንደር ያለውን የጥጥ መዳመጫ ፋብሪካን ለማቋቋም እመላለስ ስለነበር፤ ወደአገሩ ስገባ የአገሩ መደበኛ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ሲገባ በነበረው ሥርዓት ገዢውን ሔዶ እጅ መንሳት ልማድ ስለነበር የጠቅላይ ግዛቱን አስተዳዳሪ ሌ/ኮሎኔል ታምራት ይገዙን እጅ ለመንሳት ወደቢሮአቸው ሔድኩ። ይህ ሥርዓት አንድም አክብሮት ነው። አንድም ደግሞ የመጣበትን ጉዳይ አሥረድቶ የሚረዳው ነገር ካለ ያንንም ለማግኘት እንዲችል ነው። በሌላ በኩልም የደህንነት ማረጋገጫም ነበር። እንግዲህ ለዚህ ጉዳይ ሔጄ ወደቢሮአቸው ከገባሁ በኋላ ሰላምታ ተለዋውጠን ስንጨርስ ጊዜ ወስደን መነጋገር ጀመርን። ዋና ጉዳያቸውንም ሌ/ኮሎኔል ታምራት ‹‹ጃንሆይ አደጋ ቢደርስባቸው ኖሮ በማን ለመተካት አስባችሁ ነበር?›› በማለት አነሱ። በዚሁ ዓመት ንጉሡ ይበሩበት የነበረው ሄሊኮፕተር አዋሳ ላይ ሊያርፍ ሲል ወድቆ። ሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሣኤ (የሲዳማ አውራጃ ገዢ ነበሩ) ሊቀበሏቸው በአቅራቢያው ስለነበሩ መስታወቱን ሰብረው አውጥተዋቸዋል። ሌ/ኮሎኔሉ ያነሱት ይሔንኑ አደጋ ነበር። እኔ ግን ማን ሆኜ ነውና እንደዚህ ብለው የሚጠይቁኝ ብዬ ተቆጣሁ። እሳቸውም ‹‹ብርሃኑ ቆይ! ቆይ! አትቆጣ። ይሔን ሁሉ ሰው ደጅ አቆይቼ አንተን የማነጋግረው ምክንያት ስላለኝ ነው። እኔ ዘንድ መጥተህ አንድ ቀን ስለራስህ ወይም ስለዘመዶችህ ጠይቀኸኝ አታውቅም። የምታነሳው የአገርና የወገንን ጉዳይ ብቻ ነው። እኔም ዛሬ ይህን ጊዜ ይዤ የማነጋግርህ ለዚህ ነው።›› አሉኝ። እንደመሰለኝ በመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ሰበብ ታሥሬ ስመረመር ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ጋር ነበር የሚባለውን ይሰሙ ነበርና አሁንም ከተቃዋሚው ወገን አይጠፋም ብለው አስበው ነው። ለማንኛውም እኔም ከቁጣዬ መለስ አልኩ።

በዕለቱ ሊነግሩኝ የፈለጉትና ያሳሰባቸው ጉዳይ ይችን አገር (መንግሥት) ችግር የገጠማት እንደሆን ብዙ ረብሻና ዕልቂት ሊገጥማት እንደሚችል ስላሳሰባቸው መሆኑን ገልጸውልኝ መወሰድ ስላለበት እርምጃ ያላቸውን ሐሳብ እንዲህ ብለው አጫወቱኝ።

> ኢትዮጵያን የሚያስፈራት ወታደሩ የተነሣ እንደሆነ ነው። ስለዚህ የወታደሩን ኃይል ማርገብ የሚችል ነጋ ኃይለ ሥላሴ ነው። ወታደሩ ነጋን

[37] በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የምገልጸው በግል በአጋጣሚዎች ያወቅሁትን ያህል ብቻ ነው።

> ያከብረዋል፤ ይሰማዋል፤ ይቀበለዋል። ነጋ ከመቀመጫው ተነስቶ ግሩም ንግግር ማድረግ ይቻለዋል። ንብረት የሌለው ያልዘረፈና ጨዋ እንደሆነ ወታደሩ ያውቀዋል። ስለዚህም ይቀበለዋል። በእርግጥ ነጋ ጥቂት ሲቆይ ዲክታተር (አምባገነን) ይሆናል። ስለዚህ ከሁለት ዓመት በላይ መቀመጥ የለበትም። ከኋላው ደግሞ ጄኔራል አሰፋ አየነ ማድረግ ያስፈልጋል። ካለነው ሁሉ ደግሞ ሁለቱ ብቻ ናቸው በደንብ የሚስማሙት። አሰፋም ብርቱ አንባቢ፣ ስንዝር ሲጠይቁት ክንድ መመለስ የሚችል፣ ብልህና ዐዋቂ ነው።

ይሔኔ ‹‹እንዲህ ከሆኑ ለምን አሰፋ አየነ ግንባር ቀደም ሆነው አይቀርቡም? ሥልጣን ከሸዋ እጅ እንዳይወጣ ነው ትግሉ›› ብዬ ጠየቅኩ። ‹‹አይደለም! አይደለም!›› አሉና ጄኔራል አሰፋ ለግንባር የማይሆኑበትን ምክንያት እንዲህ ሲሉ ገለጹ።

> ጄኔራል አሰፋ የግንባር ሰው መሆን አይችልም። ባርኔጣውን ሰብሮ፣ ኮቱን ከኮትነትና ከካፖርትነት መለየት እስኪያቅት ድረስ አንዘርፎ፣ ኪሶቹንም ሳይቀር ከተለመደው መጠን አስፍቶ ባጠቃላይ ጅል መስሎ መታየት የሚፈልግ ነው። በዚያ ላይ እኛ ይህ ነው የማይባል ሐሳብ ለጃንሆይ በጽሑፍ ያቀረብን ከሆነ፤ እንዲቀበሉት እስከመጨረሻ እንከራከራለን። አሰፋ ግን ምርጥ ጽሑፍ አቅርቦ ጃንሆይ ሲያጣጥሉት ቁሞ አይከራከርም፤ ዝም ብሎ ይመለሳል እንጂ።

አሉና ንግግራቸውን ቀጠሉ።

> ጄኔራል ነጋ የማይሆንበት አጋጣሚ ከተፈጠረ' ደግሞ ሌላው አማራጭ ራስ አሥራተ ካሣ ነው። አሥራተም ንግግር ዐዋቂና ሰው ማግባባት የሚችል ነው። ጦሩ ግን አሥራተን እንደ ነጋ አመኔታና ከበሬታ ላይሰጠው ይችላል። ቢሆንም ያለው አማራጭ እርሱ ነው።

አሉኝ። በዚህ ግዜ እልህ ውስጥ ገብቼ ‹‹ምንም ሞያ እሠራለሁ ባልል፣ በረሃ ለበረሃ ስንከራተት እዚያው እቀራለሁ እንጂ ለአሥራተ ካሣ መንግሥት አልገዛም።›› አልኳቸው። እሳቸውም ደንግጠው ከመቀመጫቸው ተነስተው ‹‹ምንድን ነው ችግሩ›› አሉኝ። ምክንያቴን አልነገርኳቸውም። እሳቸው ግን ወዲያው ‹‹አይ ነገ ወደአሥመራ በአውሮፕላን ተጉዘን አስታርቃችኋለሁ›› አሉ። እንደዚህ ከተባባልን በኋላ ጉዳዩን እዳር ሳናደርስ ተለያየን።

የዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዙፋን መዝመሙ በብዙኃኑ እየታወቀ የመጣው ከ፲፱፻፷ዎቹ ዓ.ም. ጀምሮ ነው። ለዚህ ዋና ምክንያቱ ደግሞ የጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስን ዓይነት በውስጥ አስተዳደር የተካነ፣ ችግርን አስቀድሞ አነፍንፎ ብልኀት የሚያበጅ ባለመገኘቱ ነበር። ጸሐፌ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ የተለመደውን የጎንዮሽ አሠራር አያውቁበትም፤ የሚፈልጉትም አልነበሩም። ስለዚህ ከባህሉ ጋር የሚሔድ ዘዴ በመፍጠር ለችግሮች መፍትሔ ማቅረብ አልቻሉም። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያን ችግር አንድ አድርጎ የሚሠፋ ብልህ መሪ ታጣ። ይሄ ሁኔታ ያሳሰባቸው የመንግሥት ባለሥልጣኖች ችግሩን ለመፍታት የሰው ለውጥ እንደሚያስፈልግ ማሰብ ያዙ። እየተባባሰ የሔደውን የፖለቲካ ትኩሣት ለማብረድም

ለጊዜው አክሊሉ ሀብተ ወልድን በይልማ ደሬሳ ለመተካት ዐቀዱ። ጃንሆይ ግን ፈቃደኛ ባለመሆናቸው አክሊሉን በይልማ ደሬሳ የመተካቱ ሐሳብ ቀረ። በዚህ ዓይነት መፍትሔ ለማምጣት የሚደረገው ጥረት የማይሳካ መሆኑ እየታየ በመሔዱ ቀስ በቀስ የባለሥልጣኖቹ ስብስብ (መንዜ፣ መራ ቤቴ፣ ቡልጋ እየተባባለ) እየተቧደነ መከፋፈል ጀመረ።

በዚሁ ወቅት የአክሊሉ ሀብተ ወልድ ሥልጣን አሠራር መንግሥትን አደጋ ላይ ይጥላል ብለው ይሠጉ ከነበሩት መካከል አንዱ ደጃዝማች ፀሐዩ ዕንቁ ሥላሴ በተለይ አንዳንድ አስተያየታቸውም ይታወቅ ነበርና እንደ አፈንጋጭ ይታዩ ነበር። ለዚህ ይመስላል በ፲፱፻፷፭ ዓ.ም. መጀመሪያ አካባቢ የጐንደር ተወላጅ የነበርነውን አቶ ዳኘው (ኋላ አምባሳደርና የጐንደር ጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪ፣ ኮሎኔል ሞላልኝ በላይ ኋላ የጐጃም ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪን እና እኔን (የኦጋዴን ልማት ዋና ሥራ አስኪያጅ) አዲስ አበባ ቀጨኔ መድኃኔ ዓለም መንገድ ላይ ካለው ቤታቸው ከተመረጡ አስተናጋጆች ውጪ ማንም በሌለበት ጋበዙን። ተጋባዦች የተመረጥነው ከኋላችን የአካባቢዎቻችን ድጋፍ እንዳለን ግምት ውስጥ በማስገባት ነበር። ድግሡ የተሟላ ሆኖ ግብዣው የተደረገበት ዋና ጉዳይም የአማራውን ሕዝብ ለማስተባበር እንድንሠራ ነበር። ደጃዝማች ፀሐዩ ‹‹ከእንግዲህ ወዲህ ማንም ቢመጣ ተነሳሁ የሚለው አማራው ሕዝብ ላይ እንጂ ለይቶ የሸዋ፣ የጐንደር፣ የጐጃም አይልም። እኛም ወደድንም ጠላንም የአማራው አንገት አንድ መሆኑን ማወቅ አለብን። ስለዚህ አማራው መተባበር አለበት›› ‹አሉን። በዕለቱ በጉዳዩ ላይ ከተነጋገርን በኋላ እኛም የምንችለውን እንደምናደርግ ተስማምተን ተለያየን። መቼም በዚያ ወቅት ስለጉዳዩ በቀጥታ ያነጋገሩን ደጃዝማች ፀሐዩ ይሑኑ እንጂ፤ ሌሎች ጎላ ጎላ ያሉ የሸዋ መኳንንቶችም በተገናኘንበት ጊዜ ሁሉ በዚሁ ጉዳይ ዙሪያ ያሻርቱን[38] ነበር። ለማንኛውም ይሄም ሐሳብ የትም የደረሰ አልነበረም።

[38] ማሻረት ማለት ማንዣበብ አለፍ ሲልም ማግባባትና መባበል ማለት ነው።

## ምዕራፍ ፲

# የኑሮ ዕጣዬ

### ከእሥር ተፈታሁ

ቀኛዝማች ተፈሪ ተክለ ማርያም ከሸዋ መኳንንት አንዱ የነበሩ የፕሮፌሰር ነቢያት ተፈሪ አባት ናቸው። ቀኛዝማች ተፈሪ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ምኒልክን ያጥላሉ ነበር። ምክንያቱም እሳቸው ከሸዋ ታላላቅ ከነበሩት ከበዙ አባ ደክር ተወላጅ ሲሆኑ፣ አባታቸው ከምኒልክ ተዋግተው ስለገደሏቸው ነው። እኛ ወህኒ ቤት ስንገባ ቀኛዝማችን ያገኘናቸው፣ በመሬት ጉዳይ ተጋሪያቸውን የክብር ዘበኛ መኮንን አስገድለሃል ተብለው ፲፪ ዓመት እሥራት ተፈርዶባቸው ወህኒ ቤት ስለቆዩን ነው። ቀኛዝማች ተፈሪ እሥር ቤት ውስጥ እያሉ እንደፈለጉ ይናገሩ ነበር። ቀኛዝማች ተፈሪ ተክለማርያም የነጄኔራል ዓቢይ አበበና የነጄኔራል ደበበ ኃይለ ማርያም የቅርብ ዘመድ ናቸው። ከኮሎኔል ክፍሌ ዕርገቱ ጋርም ግንኙነት ነበራቸው። በዚህም ምክንያት በሣምንት ሦስት ቀን ወደቤታቸው መሔድ የተፈቀደላቸው ናቸው።

ከእኔ ጋር በተገናኘን ቁጥር ‹‹አንተ አረንዛ ነህ›› ይሉኛል፣ ሁሉን መሸከም ትችላለህ እንደማለት። በተለይ ‹‹ወርቅነህ ያለነገር አላስጠጋህም›› የሚለውን አባባል እየደጋገሙ ይናገሩ ነበር። ለዚህ ምክንያት የሆናቸው በተለያየ ጊዜ ለማበሳጨት ሲፈትኑኝ፣ እንደሌሎቹ አልሆን ስላልኳቸው ነው። ከዚህ ውስጥ ሌሎች የታሠሩ ጉንደሬዎችን ‹‹ቴዎድሮስ እኮ ዕብድ ነው›› ሲሏቸው ተናደው ሊገድሏቸው ይፈልጋሉ። እሳቸው ግን ለመፈተን ሆን ብለው የሚያደርጉት ነው። እኔን እንዲህ ለማድረግ ሲሞክሩ ግን ዘወትር ባልተለወጠ መንፈስ እንዴት ለምን እያልኩ የሚናገሩትን ሁሉ ለማጣራት ንግግራቸውን አስጨርሳቸው ነበር እንጂ እንደሌሎቹ ረብሻ አልፈጥርም። ስለዚህ ቀኛዝማች ተፈሪ ተክለማርያም ‹‹ብርሃኑ ቻይ ነው። አስተዋይ ነው። ግድግዳ በስቶ የሚያይ አራት ዓይን አለው›› ይሉ ነበር። ልክ እንደ ቀኛዝማች ተፈሪም የወህኒ ቤቶች አስተዳደር ረዳት ሚኒስትር አቶ ጫንያለው ተሾመም ‹‹ብርሃኑ ያንተ ነገር በጣም አስቸጋሪ ነው። እንዲህም ቢሉህ እንዲህ ያው ነህ›› ስለአንተ አስተያየት ለማወቅ ተቸገርን›› ይሉ ነበር።

እንዲህ ዓይነቶቹ አስተያየቶች በአንድ በኩል በትዕግሥት የማለፍ ችሎታዬ ማሳያ ቢሆንም፣ በእሥረኛነቴ የተለየ አትኩሮት ስላስደረገብኝ ደግሞ ችግር ፈጥሮብኛል። ይኸውም ቀኛዝማች ተፈሪ ልፈታ ሦስት ሳምንት አካባቢ እንደቀረኝ ‹‹በሸዋ ትልቅ ሰይጣን አሁን ሊለቀቅ ነው›› እያሉ ውጭ ለነ ጄኔራል ዐቢይ፣ ጄኔራል ደበበ እና ደጃዝማች ክፍሌ እርገቱ የሚያወሩትን ወህኒ ቤትም መጥተው ሲያወሩ ራሴ ሰምቻቸዋለሁ። እውነትም እሥራቴን ጨርሽ ልፈታ ስምንት ቀን ሲቀረኝ ደግሞ ቀኛዝማች ተፈሪ እንደጫዋታ አድርገው ‹‹ብርሃኑ ቢፈታም ወደ ግዞት ይሔዳል››

የሚል ጭምጭምታ አስወርተው ሰማሁ። በወቅቱ የጤና ችግር ስለነበረብኝ ምኒልክ ሆስፒታል ተልኬ እየታከምኩ ሳለሁ፤ ልፈታ ሦስት ቀን ሲቀር ፀጥታ መሥሪያ ቤት ተወሰድኩና የሕዝብ ፀጥታ ረዳት ሚኒስትሩ ጄኔራል ይልማ ሺበሺ ፪፻ ብር በወር እያገኘሁኝ ሚዛን ተፈሪ እንድቀመጥ ስለመወሰኑ እንዲነገረኝ የተጠራሁ መሆኑን ገልጸው ‹‹አሁን አስቸኳይ ሥራ አለኝ።›› ብለው ከቢሮ ወጡ። ከዚያ እኔ ስወጣ የቀድሞ መሥሪያ ቤቴ ስለነበረ የሚያውቁኝ ሠራተኞች ምን እንደተባልኩ እየጠየቁኝ ወደግዞት ትሔዳለህ አሉኝ። ‹‹እኔም እሬሳዬን እንጅ እኔን አትወስዱኝም። ባጠፋም ባላጠፋም በፍርድ ይወሰንብኝ እንደሆነ እንጂ እንዲህ በትእዛዝ የሚሆን ነገር የለም›› እያልኩ ወጣሁ።

የዛኑ ዕለት የወህኒ ቤቱ ጥበቃ ፖሊስ ቀርቶ የአዲስ አበባ ፖሊስ ተረክቦ እንዲጠብቀኝ ተደረገ። ከወህኒ ቤቱ እሥረኛ የተረከበኝ ፖሊስ አደገኛ ነው ተጠንቀቅ ስለተባለ፤ አንድ እግሬንና እጄን ከአልጋው ብረት ጋር በሰንሰለት አሠሩኝ። ይህን ያዩት ሐኪሞችም በነገሩ አዝነውና ተበሳጭተው ታካሚ እንዲህ ያለ ነገር የሚደረግ ከሆነ አናክምም አሉ። የራስ እምሩ ልጅ ባል የሆነው ዶ/ር ዘለቀ በቀለ በተለይ በዚህ ሁኔታ ያለ እሥረኛን እንደማያክሙ፣ ሕክምና እንጂ ፖለቲካ አንሠራም ብለው እሥረኛውን ውሰዱ አሉ። እንደተባለውም ታኅሣሥ ፲፭ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ.ም. ጄኔራል ይልማ ሽበሺ የፀጥታው ምክትል ኃላፊና የአዲስ አበባ ፖሊስ አዛዥ እኔን ቢሮአቸው አስጠሩኝና ዛሬ ተፈተሃል አሉኝ። ነገር ግን ነገሩ እስቲታይና እስኪረጋጋ አንተም ትንፋሽ እስትታገኝ ከአዲስ አበባ፣ ከአምቦና ደብረዘይት (ቱሪስት የሚሔድባቸው ቦታዎች ናቸው) በስተቀር ሸዋ እንድትቀመጥ ተወስኗል። ስለዚህ እጅህ ለሸዋ ፖሊስ ተሰጥቶ ሕክምናህን እስክትጨርስ ሐኪም ቤት ተመለስ ተባልኩ። አሁንም ልክሰስ እንጂ አልሔድም አልኩ። በመጨረሻ ግዞቱ ቀረና በቀን ሦስት ጊዜ እየፈረምኩ አዲስ አበባ እንድቀመጥ ተፈቀደ። ሁለት ቀን በትእዛዙ መሠረት እየፈፀምኩ ከቆየሁ በኋላ የአውቶብስ መመላለሻ ገንዘብ ስላልነበረኝ ቀረሁ። ስጠየቅም ‹‹ገንዘብ ስለሌለኝ ቀረሁ›› አልኩ። አሁንም እሺ የምትፈርመው በቀን አንድ ጊዜ ይሁን ተባለ። እሱንም ቢሆን ሁለት ቀን ተመላልሼ አቆምኩ።

ከዚህ በኋላ እንደማንኛውም ሰው ሠርቼ እንድኖር እንዲፈቀድልኝ ስል ማመልከቻ ጻፍኩ። ለዚህም መልስ በቃል ‹‹ሥራ ፈልገህ መግባት ትችላለህ›› ተብሎ በጄኔራል ይልማ ተነገረኝ። ሥራ ሳፈላልግ ወዲያው ሳቢያን ዩቲሊቲ የተባለ ትልቅ የብረታ ብረት አቅራቢ ድርጅት ሥራ ጠይቄ ተቀብለንሃል አሉኝ። ነገር ግን ሻለቃ ብርሃኔ የተባለ ከደህንነቱ ድርጅት የመጣ ፖሊስ ተናግሮ ቅጥሩ ተሰረዘ። እንደገና ፖስታ ቤቱን እየሠራ የነበረው ተቋራጭ ድርጅት ተቀበለኝ። አሁንም ሻለቃው እንዳትቀበሉት በማለቱ አንቀበልህም አሉኝ። ከዚህ በኋላ ሼል ኩባንያ የኒውስ ቡሌቲን (መጽሔት) አዘጋጅ እንድሆን ወዳጄ አቶ አላምረው ወልደ ማርያም ቢያመቻችልኝም ማክሰኞ ሥራ እንድጀምር ተነግሮኝ የነበረው፤ አርብ ከወዲሁ እንድትመጣ ተብዬ

በመንግሥት ጋር ባጋጠመ ጉዳይ ምክንያት እንደማይቀበሉኝ ነገሩኝ። ይሄን ጊዜ በጣም ስለተናደድኩ ፀጥታ መሥሪያ ቤት ሔጄ ለጄኔራል ይልማ ሺበሺ ሁለት ነፍስ የለኝም። የኔ መኖር ካልተፈለገ የሌላውን መኖር እንዴት እፈልጋለሁ? እንዲያ ከሆነ ብቻዬን አልሞትም አልኩ። በዚህ የተነሳ ሁለተኛ እንዳይደርስብህ ለሻለቃው ይነገረዋል ተብሎ ሲፈለግ በዕለቱ ሳይገኝ ቀረ። የእኔም ቅጥር እንደተከለከለ ቀረ።[1]

ከዚህ በኋላ እንዳጋጣሚ ፔፕሲ ኮላ ገና እየተቋቋመ ስለነበር፤ ቅጠሩኝ የሚል ማመልከቻ አቀረብኩ። አንድሬ ካብቴል የተባለው ፈረንሣዊ ሥራ አስኪያጅም ‹‹ላንተ የሚሆን ቦታ የለንም። ያለን ቦታ አንድ ብቻ ነው። ይኸውም ደሞዙ ፲፻ ብር የሆነ ጠርሙስ መጋዘን ኃላፊነት ነው›› አለኝ። እኔም የምጠላው ያለሥራ መቀመጥን ብቻ ስለሆነ ማንኛውንም ሥራ ለመሥራት እንደምፈልግ ተናገርኩ። እርሱ ግን ፈቃደኛ የመሆን አዝማሚያ አላሳየኝም። እንዳጋጣሚ ከእርሱ ቢሮ ስወጣ የቦርዱ ፕሬዝዳንት አቶ ጌታቸው ገብረ ዮሐንስን አገኘቼአቸው አነጋገሩኝ። ሥራ አስኪያጁ ስላለኝም ሲጠይቁኝ ትንሽ ያቅማማ እንደመሰለኝ ነገርኳቸው። እሳቸውም ሥራ አስኪያጁ የሠጋው አንተ ከመንግሥት ጋር ግጭት ውስጥ የገባህ ስለሆነ ለብድርም ለሌላም ዕክል እንዳይፈጠርበት ነው። ስለዚህ ከተቻለ አይዞህ የሚለው ሰው አቶ ተሾመ ገብረ ማርያም አሊያም አቶ ጫንያለው ተሾመን ወይም አቶ ዘውገ ወልደ ማርያምን አንዱን ብታመጣለት ይደፋፈራል›› አሉኝ። እኔም ‹‹ኸረ ሦስቱንም ማምጣት እችላለሁ›› አልኩ። በወቅቱ እነዚህ ሦስት ወጣት ባለሥልጣኖች የዐፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት አስተዳደር ከመፈንቅለ መንግሥቱ ክሽፈት በኋላ የተረጋጋ መንገድ ይዞ እንዲሔድ ብርቱ ጥረት የሚያደርጉና አቶ አክሊሉ ሀብተ ወልድን በሐሣብ የሚያግዙ የነበሩ ናቸው። በተጨማሪም ያን ጊዜ በመፈንቅለ መንግሥቱ ተሳታፊ ለነበሩ ሁሉም አጋዥና ደጋፊው ነበር። እኔም በመጠኑ እታወቅ ስለነበር፤ ሁሉም እንደሚደግፉኝ እተማመን ነበር።

ከዚህ ቀጥዬ ስለሁኔታው ለወንድሜ ለልጅ ታደሰ አያሌው (የደጃዝማች አያሌው ብሩ ልጅ) አጫወትኩት። እርሱም ወዲያው ወደ አቶ ተሾመ ገ/ማርያም እንሒድ ብሎ በመኪና ወሰደኝ። አሁን ሙሉ ባር (ሼህ መሐመድ አሊ አላሙዲን ለልጃቸው ከሠሩት ትልቅ ህንፃ) አጠገብ ጉን ባለው የአቶ ተሾመ ገብረማርያም መኖሪያ አፓርታማ ወሰደኝ። አቶ ተሾመ የፔፕሲ ኮላ ኩባንያ የሕግ አማካሪ ነበር። ከዚያም ወዲያው በመኪና ወደ ካምፓኒው ይዞኝ ሔዶ ‹‹በእርሱ በኩል ለሚመጣው ነገር እኔ እስከ ጃንሆይ የሚያደርስም ቢሆን አለሁ›› ብሎ ለሥራ አስኪያጁ ነገረው። ሥራ አስኪያጁም ‹‹ላስብበትና ዐርብ እነግርሃለሁ›› አለው። ስወጣ ለአቶ ጌታቸው ገብረ ዮሐንስ እንደመጣሁ ስነግራቸው፤ አቶ ዘውገን ብትጨምር አሉኝ እና የአቶ ተሾመ ገብረ ማርያምን ይዞታ አጠናከርኩት።

1 ሻለቃ ብርሃኔ ደርግ ከገደላቸው ፷ ሚኒስትሮች ጋር ከተገደሉት አንዱ የሆነ የፖሊስ መኮንን ነው።

በዚህ መልኩ ፔፕሲ የጠርሙስ መጋዘን ኃላፊ ሆኜ ከሥራ ማስኬጂያ ሃምሳ ብር እንዲጨመር ተደርጐ በብር ፫፻፶ ተቀጥሬ ሥራ ጀመርኩ። እንደውም አንድ ቀን መጋዘን ውስጥ ሳልገባ ከመካከለኛው ምሥራቅ፣ ከምዕራብ አፍሪካ፣ ከሰሜን አፍሪካ እና ከአውሮፓ የመጡ የፔፕሲ ኮላ ኢንተርናሽናል የሽያጭ ኤክስፐርቶችና የፔፕሲ ኮላ ዓለም አቀፍ ኩባንያ ምክትል ፕሬዝዳንቱን ጨምሮ አዲስ አበባ ስለነበሩ የሽያጭ ሠራተኞችን ማሠልጠን ጀመሩ። በዚህ ጊዜ የፔፕሲ ኮላ የአዲስ አበባ ከተማ ግማሽ ክፍል ኃላፊ ሆኖ ሊቀጠር የነበረው ሰው ድርጅቱ ደሞዝ ጨምሮ ስላስቀረኝ ልመጣ አልችልም በማለቱ በሣልስቱ የዚያን ሰው ቦታ ተክቼ እንድሠራ ተዛወርኩ። ለቦታው የተያዘው ባጀት ፬፻፶ ብር ስለሆነ ይኸው መጠን ተፈቀደልኝ።

በዚሁ ጊዜ ሥልጠና መስጠት ሲጀመር፤ ሁለቱ የአዲስ አበባ የሽያጭ ክፍል ኃላፊዎች (እኔና ጓደኛዬ) ስለሥራው የሽያጭ ኃላፊዎቹን ስንረዳ ለምጠየቀው ጥያቄ በምመልሰው መልስ የሚሰጠኝን ኃላፊነት እንደምወጣ ለመገንዘብ ቻሉ። ስለዚህ ከአዲስ አበባ ውጪ ወኪል ለማበጀትና ሽያጩን ለመግፋት በሚደረገው ጥረት እኔ የሲዳሞን ክፍለ ሃገር ሽያጭ ወኪል ለሆነው ሰው በምክርና በሐሳብ እንድረዳ፣ ለዚህም ከሽያጩ በሳጥን ግማሽ ሣንቲም እንዳገኝ ተፈቀደ። በከተማው የፔፕሲ ኮላ ምልክቶችን (ታፔላ) ፖስተሮችን በመጠጥ ቤቶችና በምቹ ቦታዎች ሁሉ መለጠፍ አስፈልጐ ስለነበር እኔና ቡድኔ በአጭር ጊዜ በጥሩ ሁኔታ ለጥፈን ጨረስን። እንዲህ ዓይነቱ የሥራ ቅልጥፍናዬ የፔፕሲ ኮላን ሹማምንት ቢያስደስታቸውም፤ በኩባንያው የሚኖረው ቆይታዬ ግን ረጅም እንዳልሆነ ይገምቱ ነበር። ስለዚህ አሁን ስለቸገረው የተቀበለው ሥራ እንጂ የሚዘልቅበት አይደለም እያሉ በጥርጣሬ ያዩኝ ነበር።

ይህ በዚህ እንዳለ በአስኮ ‹‹ሬድሲ ቻንድሪስ›› የሚል የንግድ መርከቦች ምግብና መጠጥ አቅራቢ ኩባንያ በአሰብ የፔፕሲ ኮላ ምርት ወኪል በመሆን ወስዶ ለማከፋፈል ከኩባንያው ጋር ተነጋግሮ ይስማማና አንድ ትሬንታ ኳትሮ መኪና ሙሉ ፔፕሲ ኮላ ጭኖ ከአዲስ አበባ እስከ አሰብ ተጉዞ ፳ ሣጥን ሳይሸጥ ምርቱን ይዞ ተመለሰ። የፔፕሲ ኮላ ኩባንያ ከኮካ ኮላ ኩባንያ ጋር ከባድ ውድድር ይገጥመው ነበር። በተለይ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ፋይናንስ ክፍል ባልደረባ የነበረው አቶ ብርሃኑ ኪዳኑ በአየር መንገዱ ከነበሩ ኤርትራውያን ጋር ሳይግባባ በመቅረቱ ተሰናብቶ ወጥቶ ዋናው መሥሪያ ቤት የፔፕሲ ኮላ ኩባንያ ፋይናንስና ፐርሶኔል ማናጀር ሆኖ ነበር። በዚህ አጋጣሚ በአዲስ አበባ ከተማ አብዛኛው የመጠጥ ንግድ የተያዘው በትግሪኛ ተናጋሪዎች ነበር። በተለይ አሁን የአየር መቆጣጠሪያ ክፍል ከሆነው እስከ ተክለ ሃይማኖት፤ ከዚያም ከመርካቶ መጠጥ ማከፋፈያ ራስ ስዩም ሰፈር (አሜሪካን ግቢ) እስከ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ድልድይ ድረስ ግራና ቀኝ ያሉት መጠጥ ቤቶችንና ቡና ቤቶችን የኮካ ኮላ ኩባንያ የሽያጭ ክፍል ኃላፊ በስሩ ለሚሠሩ ሁለት ሰዎች ለእያንዳንዳቸው ፫፻፶ ብር በቀን (በድምሩ ፯፻) እየሰጠ

በየመጠጥ ቤቱ እየዞሩ ኤርትራውያን ቡና ቤት ኃላፊዎችን እየተቀራረቡ የሚጠጡና የእኛን ዘር የማይወድ ፔፕሲ ኩባንያ ምርት መጠጥ እንዴት ታስገባላችሁ እያሉ በማውራትና በማጥላላት የኤርትራ ተወላጆችን በመቀስቀስ የፔፕሲኮላ ኩባንያ ምርትን እንዳያስገቡ ያደርጉ ነበር። እንዳጋጣሚ ደግሞ የፔፕሲ ኮላ ውስጥ ትግሪኛ ተናጋሪ የሽያጭ ሠራተኛ አልነበረም። ከ፳፫ መኪና ትገሬ የነበረው አንድ ተክስተ የሚባል ሹፌር ብቻ ነበር።

በዚህ ምክንያት ነበር ችግሩን ለመፍታት በፔፕሲ ኮላ ውስጥ ምክር ተደርጐ በያዝኩት ሥራ ላይ ተደራቢ ሆኖ እንድሠራ የ፻ ብር ጭማሪ ተደረጐልኝ ፐርሶኔል ሹምነቱ ለእኔ የተሰጠ። ስለዚህ በመጀመሪያ ወር ደሞዝ ከተለያየ አቅጣጫ የሚመጣው ተደማምሮ ፰፻፶ ብር ደረስኩ። እኔም በዚህ ተነቃቅቼ በአዲስ አበባ ግማሹ ክፍል ሽያጭ ኃላፊና የፐርሰኔል ሹምነቴ ከራሴ ፻፶ብር በማውጣት ሁለት ሦስት ቀን ፲፪ቱን ሠራተኞችን በከተማው ተከፋፍለን እንድንዞር አደረግኩ። ለየቡና ቤቶቹ መጠጥ የሚያስገቡና አንዳንዶቹም ባለቤቶች ጭምር ምርቱን ከቤታችሁ እንዳታስገቡ ስላሉን አላስገባንም አሉን። ስለዚህ በየቡና ቤቱ እየገባን ፔፕሲ እንጠይቅና አስተናጋጆቹ ‹‹ዋይ ትግሬ አይወዱም›› እያሉ ሲሉን፤ ‹‹ኸረ እኔ እራሴ ትግሬ ነኝ። ጐንደር ተወልጄ አድጌ ነው እንጂ፤ ይሄ የኮካኮላ ፕሮፖጋንዳ ነው አትስሙት›› እያልኩ በማሳመን ፔፕሲ ኮላን ብዙ መጠጥ ቤት ውስጥ ማስገባት ቻልን። ከዚህ በተጨማሪ የፐርሰኔል ሹም ስለሆንኩ አንድ የሽያጭ ሠራተኛ ሲለቅ ተተኪዎቹን ቅጥሮች መልከ ቀና መለሎ የሆኑትን በመምረጥ የመጠጥ ቤቶቹን ገንዘብ ተቀባዮችና ባለቤቶች እየሳቡ እንዲወዳጇቸው እየመከርኩ ላኩ። እውነትም በዚህ ረገድ ብዙ ለውጥ ተገኘ። በእኔ ክልል ብቻ ሳይሆን በሌላውም ክፍል ችግር ባለባቸው ቦታዎች እየዞርሁ ችግሮችን ለመፍታት ሞከርኩ።

ይሄ በዚህ እንዳለ የአሰቡ ችግር ስላልተፈታ አንድ መኪና ተጭኖ አብሬ ወደዚያው ሔድኩ። መጠጡን ጭኖ የሚሔደው አንድ ተግባቢ ኤርትራዊ ሹፌር በመሆኑ ቻንድሪስ ተዋዋለና ከአዲስ አበባ መውጣት ስለማይፈቀድልኝ የሾፌሩ አልጋ ላይ ተኝቼ ተደብቄ ወደአሰብ መንገድ ገባን። የአሰብን መንገድ በሙሉ ኤርትራዊ አይወድም ይባላል ለሚሉት ሁሉ ሾፌሩ ‹‹ሹም ሆኖ የመጣው ኤርትራዊ ነው›› እያለልኝ፤ እኔም የማውቃትን ትንሽ ትግርኛ ስለምችል በመጠቀም በመሸጣችን የጭነቱ ሲሶው እስቲቀር አሰብ ሳንገባ ከወዲሁ ሸጠን ጨረስን። ማታም አሰብ ከተማ የማውቃቸውን ጓደኞቼን ይዤ ፻፶ ብር ተከፋፍለን ይዘን በየመጠጥ ቤቱ እየገባን ሴቶቹን ውስኪ በፔፕሲ በማለት እንጠይቅና እነሱም ምንድነው ፔፕሲ ሲሉን አዲሱ መጠጥ ነው እያልን እያስረዳን ሳለ፤ አንዳንዶቹ ኩባንያው ኤርትራዊ አይወድም ሲሉ እኔም «እኔ እንታይዬ? አኔ ኤርትራዊ እንድዬ» ጐንደር ተወልጄ ስላደግሁ ነው እንጂ ኤርትራዊ ነኝ እያልኩ የአሰብን ከተማ ዞረን ሁሉን ሸጠን ጨረስን። ስለዚህ የፈለግነውን አሳክተን ወደ አዲስ አበባ ተመለስን።

ይህ በእዚህ እንዳለ ያኔ በፖለቲካ ምክንያት ከአገር የሚያመልጥ ሰው ሁሉ ወደ ግብፅ ይሔድ ስለነበር፤ ደጃዝማች ክፍሌ ወደአሰብ እንደሔድኩ ሲሰሙ ወደግብፅ እንዳይሔድ ልያዘው ብለው ንጉሡን ሊያስፈቅዱ ጠይቀው ነበር። ጄኔራል ይልማ በኋላ እንደነገሩኝ ንጉሡ «አይ እሱን አታውቁትም። እንኳን ጠፍቶ ሊሔድ ባህሩ ውስጥ ቢጨመር እንኳን ወጥቶ የሚመጣ ነው» አሉ። ስለዚህ መያዜ ቀርቶ ጥብቅ ክትትሉ ቀጠለ። በእርግጥ ይህ ግን ሥራዬን አላገደኝም። እውነትም መመለስ ብቻ ሳይሆን እንደገና አንድ መኪና ይዤ ወደአሰብ ጉዞ አድርጌ ተሳቢውን ቻንድሪስ ሲወስድ እኔ የሼልቶውን በየመንገዱና አሰብ ከተማ ለመጠጥ ቤቶች ሸጬ ጨረስኩ።

በዚህ መካከል የቻንድሪስ ኩባንያ ባለቤት ኢትዮያዊ የግሪክ ተወላጅ ከእኔ ጋር ብትሠራ፤ እዚያ የሚሠጡህን እጥፍ እከፍልሀለሁ አለኝ። በወቅቱ ደሞዜ ከነጥቅማ ጥቅሞቼ ፩ሺ.ህ፩፻ ብር ደርሶ ነበር። ስለዚህ ስሙ የእሱ ሆኖ የቻንድሪስን ሥራ እንድሠራ አዲስ ኩባንያ እንድናቋቁም ከአንድ ሰው ጋር አገናኘኝ። ይህ ሰው አንጀሎስ ሊቤራቶስ የሚባል ግሪካዊ ሲሆን፤ አዲስ አበባ ወህኒ ቤት ሳለሁ እርሱም ታሥሮ ፭ ዓመት አብረን ነበርን። በዚያን ጊዜ እሱን በወህኒ ቤቱ ኢንዱስትሪ ክፍል የሂሳብ ክፍል ሹም አድርጌ መደብኩት። የወህኒ ቤቱን ኢንዱስትሪ ክፍል ሳደራጅ በሐሣብ እንስማማ ስለነበር፤ ስንፈታ ‹‹እኔና አንተ ለሰው መገዛት /መቀጠር የለብንም፤ ለራሳችን መሥራት አለብን›› እያለ ደጋግሞ ያጫውተኝ ነበር። አሁን በዚህ ዓይነት ስንገናኝ ትንቢቱ ሲፈፀም ነው ብሎ ደስ አለው። እንዳለውም አስፈላጊውን ነገር ሁሉ እርሱ አሟልቶ «የኢትዮጵያ ኮሚሽን ኤጀንሲ» የሚል ቢሮ ከፍተን እንድንሠራ ጠየቀኝ። እኔም ከፔፕሲ ኮላ ተሰናብቼ ወጣሁ። በዚህ ጊዜ ደሞዜ ፩ሺ.ህ፱፻፶ ብር (በዓመት ከሦስት ወር ውስጥ ወደስምንት ጊዜ በደሞዝ አድጌ) ደርሶ ነበር። እንደተባለው የራሳችንን የንግድ ፈቃድ አውጥተን ሥራ ጀመርን።

ይህ በዚህ እንዳለ እኔ ከእሥር ቤት የወጣሁ ስለሆነ ቅርስ አልነበረኝም። ፲፱ቱ ጓደኞቼ ለባሌቤቴ ከሠሩት ቤት (ቦሌ የሚገኝ) አንስቶ ፒያሳ ደርሶ መልስ ፷፭ ሳንቲም ነበር። ስድስት ወር ሙሉ በአዲሱ ኩባንያ ስንሠራ ምንም ቤሳ አላገኘንም ነበር። የደርሶ መልስ ፷፭ ሳንቲም ስላጣሁ ለምሳ ወደቤት አልሔድም ነበር። ጠዋትና ማታ በእግሬ ነበር የምመላለሰው። ስለዚህ ተራ የድለላ ሥራ ሳይቀር ለመሥራት ዝግጁ ነበርን። የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወንበርና ጠረጴዛ ሲሸጡና ሲገዙ በዕቃው አምራቾችና በገዢዎች መካከል እደልል ነበር። በዚህ መልኩ ከሠራነው የመጀመሪያ ገቢያችን ፱ብር ከ፺ ሳንቲም ነበር። በሁለተኛው ቀን እዚያው መሥሪያ ቤት የጨረታ ዋጋ አቅርበን ኮሚሽን ፪፻፵ ብር አገኘን። እዚህ ላይ እያለን በ፲፱፻፷፩ ዓ.ም የቴሌኮሙኒኬሽን የመጀመሪያው ትልቅ ጨረታ የ2ሚሊዮን ፩፻ሺ.ህ ብር ኬብል ከእሥራኤል ለመግዛት ጨረታን በማሸነፋችን ድርጅታችንም እኛም ከፍተኛ ውጤት አገኘን። እሱ ራሱ የራሱ ታሪክ ያለው ነው።

የጨረታውን መውጣት እንዳወቅን ሰነዱን ገዝተን ወደተለያየ አገር ኩባንያዎችና ድርጅቶች ስንልክ ለካ The Electric Wire and Cable Company of Israel, Haifa ለሚባልም ኩባንያ ልከን ኖሮ እኛ ሳናውቀው ተወዳድሮ ያሸንፍና አቶ በቀለ ከበደ በጊዜው የኢትዮጵያ ቴሌኮም ቴሌፎን ዲቪዥን ኃላፊ ስልክ ደውሎ ሦስት ነገር ካላብራራችሁ አሸናፊነታችሁን ልንሰርዘው ነው አለኝ። ስለዚህ ወዲያው ወደቴሌኮምኒኬሽን ሔጄ አቶ በቀለን ሳናግረው (እኔ ቴክኒካል ስኩል እርሱ እንጂነሪንግ ኮሌጅ ተማሪ እያለ እግር ኳስ ጨዋታ ላይ ተጋጭተን ስለነበር ቂም ይዞ) በአግባቡ እንዳያናግረኝ ገርጠጥ አለብኝ። ስለዚህ የአዲስ አበባ ሪጅናል ኦፊስ ማናጀር የነበሩትን አቶ ግርማው እንግዳየሁን ሔጄ ‹‹ለውጪ ሰው ከሚሰጥ እኔ እሥር ቤት ቆይቼ የወጣሁ ነኝ ለባዕድ ከምትሰጡት ለእኔ ለወገናችሁ ብትሰጡኝና ብጠቀም ምናለ? ጥያቄአችሁ ግልጽ ሆኖ ቢነገረኝ›› ብዬ አመለከትኩ። አቶ ግርማውም ወደ አቶ በቀለ ቢሮ ይዘውኝ ሔዱና አቶ በቀለን ‹‹ጥያቄውን ጻፍና ስጠው›› ብለው አዘዙልኝና ተጽፎ ተሰጠኝ። ስለዚህ ለእሥራኤሉ ኩባንያ በቴሌግራም አሳወቅኩኝ።

በመልእክቱ መሠረት የኩባንያው ሥራ አስኪያጅና የማምረቻ ክፍሉ ሥራ አስኪያጅ በነጋታው አዲስ አበባ እንደሚመጡ በቴሌግራም አሣውቁንና በተባለው ቀን መጡ። እነርሱን ተቀብለን አቶ በቀለ ዘንድ ወሰድናቸው። ኩባንያው በአውሮፓ ደረጃ የሚታወቅ ሲሆን፤ የአቶ በቀለን ጥያቄም በአግባቡ ስለመለሰ ሁኔታውን አቶ ግርማውም መስማት አለበት ተብሎ እዚያም ሲያብራራ ሙያዊ ችሎታውን በከፍተኛ ደረጃ በሚያሳይ መልኩ ሆኖ ስለተገኘ፤ አቶ ግርማው ተደስተው ጨረታውን አሸንፋችኋል ብለው ብሥራቱን እዚያው ነገሩን። ከዚህ ግብይይት ፻፳፮ ሺህብር ለሁለት አገኘን። በዚህም ምክንያት ፭፭ ሣንቲም አጥቼ በየቀኑ ፲፬ ኪ.ሜ በእግሬ በባዶ ሆድ ስኳትን የነበርኩት ዛሬ ድረስ የምጠቀምበትን ፔዦ ፎር ኦ ፎር ለመግዛት ቻልሁ። ሥራው በዚህ መልኩ እየለማ ቢሔድም የኃይለ ሥላሴ መንግሥት እየተዳከመ በመምጣቱ አንጀሎ ሊበራቶስ ወደ ዛምቢያ ሲሔድ እኔ ለብቻዬ ሥራዬን ቀጠልኩ። ፒያሣ አሁን የማዘጋጃ ቤት ትልቁ ፎቅ ከተሠራበት ሕንፃ ሥር ካሉት ሱቆች በኋላ ሐጂ ራሕመት ወርቅ መሸጫ ከሆነው ጐን «የኛ መደብር» የሚል ዘመናዊ ልብስ መሸጫ ሱቅ ከፈትኩና ግሩም ሥራ መሥራት ጀመርኩ። በዚህ መልኩ በገቢዬ በደንብ እየደረጀሁ መጣሁ።

# ጎንደርና አካባቢዋን በማልማት ዙሪያ አንዳንድ አስተዋፅዖ ማድረጌ

የአገር ኩራትና ክብር የታሪክ ማማ የሆኑትን የዐፄ ቴዎድሮስ ዳግማዊ እልፈት መቶኛ ሙት ዓመት እንደሚከበር ሲነገር፤ እኔም በዓሉን በዕለቱ መጋቢት ፳፫ ቀን ፲፱፻፷ ዓ.ም. በቦታው በመቅደላ ለማክበር የሚሄዱ ተጓዦችን በማሰባሰብ በአዲስ አበባ ከመስከረም ፲፱፻፷ ዓ.ም. እስከ መጋቢት ወር አጋማሽ ድረስ ቅስቀሳ አድርጌ ብዙ ሰው ተመዘገበ።

ለመቅደላ፡ጉዞ



*በ፲፱፻፷ ዓ.ም. መቅደላ የተጓዘው ቡድን*

*ከግራ ወደ ቀኝ አቶ ባዩ ቦጋለ፣ አቶ ሚሊዮን ተሰፋዬ፣ ከመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ኮሚሽን ደጃዝማች ዓለምሰገድ በዛብህ (የአልጣሽ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ ከፓርላማ)፣ አቶ ብርሃኑ አስረስ (ባለግል ድርጅት)፣ አቶ አበበ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር አቶ ዳኘው ወልደሥላሴ፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አቶ አሰፋ አዘዘው፣ ከጠቅላይ ፍ/ቤት አቶ በሪሁን ዓለማሁ፣ ከመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ኮሚሽን አቶ ታደሰ ዘለቀ፣ የሽመልስ ሀብቴ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ፊትአውራሪ መንገሻ በዛብህ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር (የአልጣሽ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ)*

ለተጓዥነት የተመዘገበው ሰው ቁጥር መብዛት ግን የደህንነት ጉዳይ ስላስነሳ ተጓዦቹ በመንገዳችን ላይ ችግር እንዳያጋጥመን ገዢው ልዑል አልጋወራሽ አስፋወሰን ኃይለ ሥላሴ የድጋፍ ደብዳቤ እንዲያዙልን በጽሑፍ ጠየቅሁ። የእልፍኝ አስከልካዩ ብርጋዴር ጄኔራል በቀለ ማኅተመ ሥላሴ ማመልከቻችንን ለልዑልነታቸው አሳይተው ትብብር እንዲደረግልን የተፈቀደ በመሆኑ እጅ እድነሳ እንዲፈቀድልኝ ጠይቁ ተፈቅዶልኝ፤ ተልዑልነታቸው ቢሮ ገብቼ እጅ ነሳሁ። ልዑልነታቸው ስለጉዞው ፕሮግራም ጠይቀውኝ ዝርዝሩን ገለጽኩ። በመግለጫው መደሰታቸውን ከተረዳሁ በኋላም በኮሎኔል ወርቅነህ አማካኝነት በቤተመንግሥቱ ማክሰኞና ሐሙስ እሰጥ የነበረውን መግለጫ አነሳሁላቸው። በሁኔታው ይባስ ተደስተው ፊታቸው እንደፀሐይ አበራ። ወዲያውም ጄኔራል በቀለ አብረውን ስለነበሩ ዓይናቸውን ወደጄኔራል ዘወር



*በ፲፱፻፷ ዓ.ም. መቅደላ የተጓዘው ቡድን*

*ከግራ ወደ ቀኝ አቶ ባዬ ቦጋለ፣ አቶ ሚሊዮን ተስፋዬ፣ ከመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ኮሚሽን ደጃዝማች ዓለምሰገድ በዛብህ (የአልጣሽ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ ከፓርላማ)፣ አቶ ብርሃኑ አስረስ (ባለግል ድርጅት)፣ አቶ አበበ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር አቶ ዳኘው ወልደሥላሴ፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አቶ አሰፋ እዘዘው፣ ከጠቅላይ ፍ/ቤት አቶ በሪሁን ዓለማሁ፣ ከመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ኮሚሽን አቶ ታደሰ ዘለቀ፣ የሽመልስ ሀብቴ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ፊትአውራሪ መንገሻ በዛብህ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር (የአልጣሽ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ)*

አደረጉ። ጄኔራል በቀለም ወዲያው ወጡና የቢሮውን በር ዘጉ። ብቻችንን ስንሆንም፣ ከመፈንቅለ መንግሥቱ በፊት ደብረዘይት ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ጋር ሲገናኙ፣ እኔ አብሬው እዚያ እንደነበርኩ ገለጽኩላቸው። ይህን ጊዜ የበለጠ ሀዘንና አግራሞት በተቀላቀለበት ስሜት ትክ ብለው አዩኝና ‹‹በል እየመጣህ እንድትጠይቀኝ፣ አሁን ለጠየቅኸው ጉዳይ በቀለ ለእንደራሴው ደብዳቤ እንዲጽፍ፣ በስልክም እንዲነግር እንነግረዋለን›› ብለው እጅ ነስቼ ወጣሁ።

ባሰብነው መሠረት ብዙ ሰዎች ለተጓዥነት ተመዘገቡ። ጊዜው እየተቃረበ ሲሔድ እንሔዳለን ያሉት ሰዎች ቁጥር ሠላሳ ሰባት ኢትዮጵያውያንና በብሪቲሽ ካውንስል በኩል የተቀሰቀሱ አሥራ ሰባት እንግሊዛውያን መሆናቸው ታወቀ። ጉዞው ሊጀመር ሲል ግን የኢትዮጵያውያኑ ተጓዦች ቁጥር ወደ አሥራ ሁለት ሲወርድ የእንግሊዛውያኑ ተጓዦች ቁጥር ከአሥራ ሰባት ወደ ሰባት ከመውረዱም በላይ ከኢትዮጵያኑ ተጓዦች ተለይተው ከበዓሉ ቀን በኋላ ስምንት ቀናት አሳልፈው እንደሚሔዱ ከብሪቲሽ ካውንስል (ላይብራሪ) ተነገረኝ። በመጨረሻም እኔ ለጉዞ በቆረጥነው ቀን አሥሩ ኢትዮጵያውያን ተጓዦች ወደደሴ ተጓዥ በሆነ በአንበሳ አውቶብስ ለመሔድ ቲኬት ቆርጠን ተሣፍረን ጉዞ ጀመርን። ከሰዓት ላይ ደርሰን ደብረሲና ምሳ በላንና ጉዟችንን ቀጠልን። ከዚያ አጣዬ ከተማ ልንደርስ ጥቂት ሲቀረን መስኩን ጨርሰን ወደ ዳገቱ ስንቃረብ ሹፌሩ እንቅልፍ ወስዶት ኖሮ መንገድ ስቶ አንድ ትንሽ ድልድይ ያላት ኩርባ ላይ ስለወጣ ብዙ ሰው ተደናገጠ። በዚህ ሁኔታ ተጉዘን አመሻሽ ላይ' ደሴ ገብተን አደርን። በማግሥቱ ጠዋት መንገዳችንን ለመቀጠል ስንል ግን በደረሰው ሁኔታ ከተደናገጡት ሰዎች ደጃዝማች ዓለም ሰገድ በዛብህ የአልጣሽ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ፣ አቶ ዳኘው ወልደሥላሴ (ኋላ አምባሳደርና የጐንደር አስተዳዳሪ)፣ አቶ አሰፋ አዘዘው የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል፣ አቶ ታደሰ ዘለቀ (የታሪክ ምሑርና የሺመልስ ሐብቴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር) ‹‹ወፍ[2] አላወጣንም›› ብለው ወደአዲስ አበባ ተመለሱ። እስከመጨረሻው የዘለቅነው መቅደላ ደርሰን ታሪካዊውን ቦታ ጐበኘን።[3]

ዐፄ ቴዎድሮስ ሽጉጣቸውን ጠጥተው ሲወድቁ፣ በዚያ የነበሩ ሰዎች አንተርሰዋቸው ነበር የምትባለውን ድንጋይ በጊዜ ብዛት በማረሻ እየተገፋች ከቦታው አሥር ሜትር ያህል ርቃለች ብለው ግራዝማች ስለገለጹልን፣ ወደነበረችበት ቦታ መልሰን ዙሪያውን በካብ አጠርናት። የመቃብራቸውም ሁኔታ በእጅጉ የተጣለ እንደነበር ታዝበናል። ዐፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን ከሰዉ በኋላ ቀብራቸው በመቅደላ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን እንዲሆን ተሞክሮ በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ቀኖና መሠረት ራሱን የገደለ ክርስቲያን ሰው በቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ

---

[2] *ገዱ ጥሩ አይደለም ለማለት ነው።*
[3] *አስጎብኚያችን ግራዝማች እንደሻው በታሪኩ ዙሪያ ልቅም ያለ ዕውቀት ስለነበራቸው ጉብኝታችንን ጥሩ አድርጎልናል*

መቅበር ክልክል ስለሆነ፣ ካህናቱ ቀብሩን በደብሩ ግቢ እንዲሆን ሳይፈቅዱ ቀሩ። በዚያው አምባ በምትገኘው ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ለመቅበር ቢሞከርም የዚያ ደብር ካህናትም ፈቃደኞች ባለመሆናቸው በሁለቱ አድባራት መኻል በነበረ ክፍት ቦታ ተቀበሩ።



*የዐፄ ቴዎድሮስ መቃብር በመቅደላ*[4]

ከጐበኘናቸው ታሪካዊ ቦታዎች አንዱ ገብርዬ የወደቀበት አምባ ነበር። አምባውን ከሩቅ ያመለከቱን አስጐብኚያችን ግራዝማች እንደሻው እንዳመለከቱን ገብርዬ የወደቀው ከአምባው ወገብ ላይ ሲሆን፣ ሲወድቅ ተደግፎባት የነበረችው ዛፍም እስከዛሬ ድረስ እዚያው ትገኛለች። ገልሞ በደቡብ ምዕራብ የተራራው ወገብ ላይ ተመቶ የወደቀበትን ቦታም እንዲሁ ከሩቅ አሳይተውናል።

*[4] ሰውየው በእጁ የሚያመለክተው የዐፄ ቴዎድሮስን መቃብር ነው። አጋጣሚ ሆኖ የዐፄ ዮሐንስ ፬ኛ የወደቁበትን ሥፍራና መቃብር እንደዚሁ በመተማ ሽመለ ጋራ በተባለው ቦታ ምልክቱ በጊዜ ብዛት እንዳይጠፋ ዙሪያውን በድንጋይ አሣጥሬዋለሁ። በአጋዴንም፣ ቆራሔ፣ ላይ የደጃዝማች አፈወርቅ ወልደ ሰማያት የወደቁበትን መቃብር ከሥራ ጓደኞቼ ጋር በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. በድንጋይ አጥረነዋል። የቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣኖችና ድርጅቱ በዚህ ረገድ መሥራት ያለባቸውን ልብ ያሉ አለመሆኑንም በተደጋጋሚ ታዝቤአለሁ።*



*የዐፄ ቴዎድሮስ መቃብር በመቅደላ*[4]

## የጐንደር ጥጥ መዳመጫ ፋብሪካን መመሥረት

በጐንደር በልማት ላይ በመሳተፍ ወገኖቼን ለመርዳት የቻልኩበት አጋጣሚ ከኑሮ እጣዬ ዋንኛው የደስታዬ ምንጭ ነበር። ለዚህ ምክንያት የሆነኝ ደግሞ የታዋቂው የፊልም ባለሞያና ምሑር የፕሮፌሰር ኃይሌ አባት የሆነው ገሪማ ታፈረ ነው። ገሪማ ታፈረ በትውልድ የወሎና ጐንደር ተወላጅ ሲሆን ከዚህ ወይም ከዚያ ሳይባል ሁል ጊዜ ኢትዮጵያዊነቱን የሚያጐላ ነበር። ጐንደር በመንፈሳዊ ትምህርት ላይ ሳለ ኢትዮጵያ በፋሽስት በመወረሯ ትምህርቱን ትቶ በውጊያ ተሳትፎ ከጀመረ በኋላ የተላበሰውን መንፈሳዊ ባህሪውን ተጠቅሞ የአርበኞች መሪዎች ባሉበት ከሱዳን በኩል የሚመጣውን መልእክት ለአርበኞች ባሉበት ሁሉ



*መቶ አለቃ ገሪማ ታፈረ*

ማድረስና በአርበኞች መካከል ግኙነት መፍጠር ላይ በማተኮር አስተዋፅዖ ያደርግ ነበር። በየጎራው ከነበሩ አርበኞችም ወደሱዳን የሚመለሰውን መልእክትም እንዲሁ ሱዳን ለሚገኘው የአርበኞች መገናኛ ቢሮ በሚለብሰው የምንኩስና ቆብና ደበሎ ውስጥ እየሰፋ ወስዶ ያደርስ ነበር። ገሪማ ታፈረ ሶባት ላይ ለኢትጵያውያን በተቋቋመው የተሐድሶ የጦር ትምህር ቤት ገብቶ ሠልጥኖ ኋላ ሌ/ጄኔራል ከሆኑት ከከበደ ገብሬ ጋር አብሮ በመቶ አለቅነት ተመርቋል። ጃንሆይ ወደአገር ሲገቡም አብሮ አጅቦ ገብቶ ከስደት የተመለሱት የጦር መኮንኖች ባረፉበት አሁን የአውራ ጐዳና ዋና መሥሪያ ቤት በሆነው ግቢ የነበረ የጣሊያን ጦር መኮንኖች ማረፊያ ከመቶ አለቃ ከበደ ገብሬ (ኋላ ሌ/ጄኔራል) ጋር በአንድ ክፍል ተመድቦ ይኖሩ ነበር። ኋላ ብርጋዲዬር ጄኔራልና የፖሊስ ሠራዊት ዋና አዛዥ የሆኑት ይልማ ሺበሺ ደግሞ ያንጊዜ በሱ ምድብ አምሣ አለቃ ነበሩ።

ገሪማ ሕዝብን የበለጠ ለማገልገል በሠራዊቱ ውስጥ ከመቀጠል ወደጐንደር መመለስን መርጦ ጐንደር ገባ። እዚያ ከደረሰ በኋላ የሀገር ፍቅር ማኅበር ድርጅት ከሲኒማ ቤቱና አሁን የሰልፍ አደባባይ መኸል አቋቁሞ ስለአገር ፍቅርና ስለሕዝብ አንድነት እንዲሁም ስለመልካም አስተዳደር ያስተምር ነበር። እሱና እንደ እሱ ከዘመቻው የተመለሱ ሌሎችም በማኅበሩ ሲያስተምሩ የሚዘምሩት መዝሙር ነበረ። እኛም ትምህርት ቤት በነበርንበት ጊዜ አቶ አያሌው ደስታ የበጌምድርና ስሜን



መቶ አለቃ ገሪማ ታፈረ

ጠቅላይ ግዛት ትምህርት ቤቶች አስተዳዳሪ የነበሩት ከ1938 ዓ.ም. ጀምሮ በሳምንት ለሁለት ቀናት መላውን ተማሪ ያዘምሩ ነበር።

፩ ተነሱ ታጠቁ ኢትዮጵያውያን
እንጀምር ሥራ በስመ አብ ብለን
ርቀው ሔደዋል ጓደኞቻችን
እንድረስባቸው በጣም ተፋጥነን

፪ እናት ኢትዮጵያ ውዲቱ ውዲቱ
በሦስቱ ቀለማት የተሸለምሽቱ
ነፃነት የሚሸር ቢመጣብሽ ብርቱ
ደማችን ይፈሳል አይቀርም በከንቱ

ገሪማ ከሀገር ፍቅር ጋር በተያያዘ ስሙ ሁል ጊዜ ይነሳል። እንደውም የጐንደር ተወላጅ በአስተዳደሩ ችግር ሲደርስበት ... ወይ አገሬ አሉ አባ ገሪማ! እያለ በመዝሙር ያሰማውን ይጠቅሳል።

ገሪማ ሲነሳ የማይረሳ አንድ ታሪክ አለ። ለጐንደር የመጀመሪያ ገዥ ሆነው የተሾሙት አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ነበሩ። የጣሊያን አስተዳደር ቤተመንግሥቱን አስጊጦበት የነበረውን የመዝጊያና የመስኮት ከፈይ (ቬልቬት) መጋረጃ፣ የብራና ወርቅ ቅብ ሹካ፣ ማንኪያ፣ ሳህን፣ ጭልፋና የመሳሰሉ የቤተ መንግሥት መገልገያ የክብር ዕቃዎችን በመኪና ጭነው ወደወሎ ሊወስዱ ሲሉ ገሪማ ቀድሞ ትግሬ መጮኺያ[5] በሚባለው ተራራ ስር በወገራ መውጫ በር ላይ መትረስ ጠምዶ መኪናዎቹን አላሳልፍ አለ። ከብዙ ውዝግብ በኋላ በመጨረሻ እርሱ ተይዞ መኪናዎቹም መንገዳቸውን ቀጠሉ። ለምን እንዲህ እንዳደረገ ሲጠየቅ የጐንደር ቤተመንግሥት ክብር አይወድለትም ወይ? የሚመጣው ገዥስ የተዋበ ቤተመንግሥት አያስፈልግወም ወይ? ለምን ዕቃው ይሄዳል? በሚል መሆኑ ታወቀ። በዚህ ቂም ተይዞበት በዓይነ ቁራኛ ሲጠበቅ ከቆየ በኋላ የትምህርት ሚኒስቴር ባልደረባ ሆኖ እንዲሠራ ተመደበ።

በዚህ ጊዜ ገሪማ በየቦታው የሚያገኘውን ልጅ ሁሉ ትምህርት ቤት ገብተው እንዲማሩ በቁንጥጫ ጭምር ያበረታታ ነበር። ተማሪ ቤት ገብተው ሲዋልጉ ሲያገኝ ደግሞ ይቆጣ ነበር። ሌላው ቀርቶ ተማሪ የሆኑ ልጆች ወደአንድ ቦታ ሲላኩ፤ አልሔድም አባ ገሪማ ያገኙኝ እንደሆነ ይቆጡኛል፤ ይቆነጥጡኛል ይሉ ነበር።

---

[5] በጐንደር ዘመነ መንግሥት ከትግራይ የሚመጡ ባለጉዳዮች ከተናጠል ይልቅ በሕብረት ጉዳያቸውን ለመንግሥት ለማሰማት ቶሎ እንዲፈቀድላቸው አቤት ባዮች የፈጠሩት ዘዴ ነበር። ይህም ባለጉዳዮች ፊት ለፊት ካለው ተራራ ላይ ሆነው እግዚአብሔር ያሳይዎ! እግዚአብሐየር ያሳይዎ!" እያሉ በኅብረት በመጮህ ተራራው ለቤተመንግሥቱ ትይዩና ቅርብ ስለሆነ ድምጹን የሚሰሙት ንጉሥ አቤት ባዮቹን አምጡና አቅርቧቸው ይሉና ሁሉም በአንድ ጊዜ ቀርበው የየግላቸውን ጉዳይ አሰምተው ውሳኔያቸውን አግኝተው በቶሎ ይመለሳሉ። ይህን ዘዴ የትግራይ ባለጉዳዮች ደጋግመው ስለተጠቀሙበት ተራራው ትግሬ መጮኺያ እየተባለ መጠራት ተለምዶ እስከደርግ መምጣት ድረስ በዚህ ስም ይጠራ ነበር።

ከመተማ እስከቋራ የሚገኙትን ጉሙዞችም ትምህርት አግኝተው ኢትጵያዊነታቸውን እንዲያጠነክሩ ድንበሩንም እንዲጠብቁ አሥራ አንድ የሚሆኑ ወጣቶችን ጉንደር አምጥቶ እየረዳ በማስተማር ኋላ ወደ አካባቢያቸው ተመልሰው በተለያየ ኃላፊነት እንዲሠሩ አመቻችቷል። በወቅቱ በሱዳን በኩል ድንበር የሚጠብቅ ወታደር ስላልተመደበ ድንበር መጠበቁ የአገሬው ኃላፊነት ነበር። ጉምዞቹን ለዚህ ዐላማ ማዘጋጀት የገሪማ ታፈረን ለአገር አሳቢነትና አርቆ አሳቢነቱ ምን ያህል እንደነበር ያሳያል። እኛን በቅርብ የሚያውቀንን ያገር ተወላጆችንም ከመተማ እስከ ቋራ ድረስ ያለውን በሥራ ላይ ያልዋለ ለም መሬት ማልማት እንደሚገባን ስለመከረን፤ እንደምክሩ ለአስተዳደሩ ማመልከቻ አስገብተን በመጠየቃችን እሱ ራሱ ወኪላችን ሆኖ ከእኔ ጋር ጓደኞቼን ጨምሮ ለእያንዳንዳችን አንድ አንድ ጋሻ መሬት እንድናገኝ በማድረጉ ማኅበር አቋቁመን የእርሻ ሥራ እንድንጀምር አበረታቶን ጀመርን።

አቶ ገሪማ ታፈረ በጣም የምንወደውና የምናከብረው ሰው ሲሆን፤ የሚያቀርበንን ያገር ተወላጆች ፊታችንን ወደትውልድ አገራችን በማዞር አንዳንድ የልማት ሥራ እንድናካሒድ በዚያውም ስለድንበሩ አጠባበቅ እንድናስብ አጥብቆ ያስጠነቅቀንና ይመክረን ነበር።

## ለውጥ በሁመራ

በዚህ ጊዜ የወልቃይት ጠገዴ ገበሬዎች ሰሊጥ ማምረት ቢጀምሩም በማምረቻ መሣሪያዎች እንደልብ አለመቅረብ እና በሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ማጣት ምክንያት በመመረት ላይ ያለውን ምርት አስቀድመው ለአሥመራ ባለሀብት አበዳሪ ነጋዴ በቅድሚያ ሽያጭ፣ ምርቱ ሲደርስ ኩንታሉን ሰሊጥ ከ፳፰-፴ ብር ዋጋ በማስረከብ የድካማቸውን ተገቢ ዋጋ እንደማያገኙ ተደጋግሞ ሲወራ እሰማ ነበር። የእናቴ እናት አባት (አያቴ) ቄስ ገበዝ ዓለሙ በወልቃይት የኩሊታ ማርያም ተወላጅ በመሆናቸው ተጐጂዎቹ ወገኖቼ ነበሩ። "ትንሽ ሥጋ እንደመርፌ ትወጋ" እንዲሉ አሠራሩ ያሳዝነኝ ስለነበር፤ በአንድ ወቅት ከአቶ ዳኘው ወ/ሥላሴ (የዚያው አካባቢ ተወላጅ በኋላ አምባሳደር እና የጉንደር አስተዳዳሪ) ከነበረ አብሮ አደግ ወንድሜ ጋር ተያይዘን ሁመራ ሔደን በሁመራ በጣም ከታወቁት ገበሬ ከፊታውራሪ ሠረበ ለማ (የወ/ሮ ዝማም ከበደ ባለቤት የአቶ ዳኘው ወ/ሥላሴ የአክስት ልጅ) ቤት አረፍን። በአገሩ ልማድ አንድ እንግዳ ከውጭ መጥቶ ከአንድ ገበሬ ቤት ሲያርፍ ጐረቤት እና ወዳጅ ሁሉ የሚበላና የሚጠጣ መስተንግዶ ያመጣልና ከመጣው ጐረቤት ጋር ስንጨዋወት ከላይ የተጠቀሱትን የአሠራር ችግሮች በስፋትና በጥልቀት ተረዳሁ። በዚህ ምክንያት አዲስ አበባ እንደተመለስኩ የዚሁ አካባቢ ተወላጅ እና በፓርላማ የዚሁ አካባቢ ሕዝብ ተወካይ ከነበሩት እና በኋላ የገንዘብ ሚኒስቴር ባልደረባ ከሆኑት ከታወቁት ከቀኛዝማች ኃይለማርያም ደሴ ጋር ተገናኝተን ስለ ችግሩ መፍቻ ስንወያይ የልማት

ባንክ ፕሬዝዳንት ለሆኑት ለአቶ ተካልኝ ገዳሙ ብናማክራቸው ጥሩ እንደሚሆን ሐሳብ ተነስቶ ተስማማን፡፡

አቶ ተካልኝ ገዳሙም ችግሩን ከሰሙ በኋላ የሚከተለውን ሐሳብ ሰጡን፡፡ ከልማት ባንክ ገንዘብ ለመበደር ገበሬዎቹ የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማህበር ማቋቋም እና ሕጋዊ ሰውነት ማግኘት አለባቸው፡፡ ይህን ለማደራጀት ጊዜ የሚፈጅ ከሆነ ግን ለጊዜው "ሴሪስ" ከተባለው ኩባንያ ጋር በመዋዋል በኩባንያው አማካኝነት የአጭር ጊዜ ብድር ማግኘት እንደሚቻል መከሩን፡፡ ምክንያቱም ኩባንያው ተበድሮ ለገበሬው ሊያበድር ስለሚችል ማለት ነው፡፡ ይህንንም ለማድረግ አቶ ሙሉጌታ ገብረወልድ የልማት ባንክ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ አቶ ብሥራት ጀማነህ የሴሪስ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ፣ ቀኛዝማች ኃይለማርያም ደሴ እና እኔ ወደ ሁመራ ሔደን ስለዐላማውና አሠራሩ ለገበሬዎቹ እየዞርን ባስቸኳይ የወልቃይት ጠገዴ ሁለገብ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማኅበር እንዲያቋቁም ለፈፍን፡፡ በዚህ መሠረትም ፳፰ የሚሆኑ ፈቃደኛ ገበሬዎች ወዲያው ተሰብስበው የኅብረት ሥራ ማኅበሩን አቋቁመው ለጊዜያዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደጃዝማች ታዬ ጉላን፣ ፊታውራሪ ሠረበ ለማን፣ ፊታውራሪ ሺ ወንድም ናደውን፣ መልአከ ሰላም (ቄስ) ሲሳይ አየለን፣ አቶ አብድልቃድርን (ወዲ ብላታ)፣ አቶ ተስፋዬ አንሳይንና ግራዝማች ብርሃኔ ዘነበን መረጡ፡፡ የማኅበሩ መመሥረቻና መተዳደሪያ ደንብም ወዲያው ተዘጋጅቶ ለጊዜው እያንዳንዱ አባል አንድ አንድ ሺ ብር (በድምሩ ፳፰ሺ) ብር ስላዋጣ፤ ይሄ ለአጥኚዎቹ ጥሩ ምልክት ሆነ፡፡

ከዚህ በኋላ አጥኚው ቡድን የተጀመረውን እንቅስቃሴ ደገፎ ራፖሩን ጻፈ፡፡ በዚያው ዓመት በዚሁ ማኅበር ዋስትና ለሥራ ማስኬጃ የሚሆን ብር ፱፻፲፭ ሺህ (ዘጠኝ መቶ አሥራ አምስት ሺህ) ለገበሬው ብድር ሰጠ፡፡ ምርቱንም በማኅበሩ ስም አንድ ላይ ተሰብስቦ ተይዞ፤ በዚያው ዓመት የአንድ ኩንታል ሰሊጥ ዋጋ ፵፩ ብር ደረሰ፡፡ ለቀጣዩ ሥራ አሚራን ከተባለ የእሥራኤል የእርሻ መሣሪያዎች አቅራቢ ድርጅት ጋር ተነጋግሬ ኩባንያው ከእኔ ጋር አጥኚ ቡድን ልኮ እርሻው ከታየ በኋላ ለማኅበሩ እና ወደ ማኅበሩ ይገባሉ ለተባሉ ግለሰቦች በዱቤ አስፈላጊ የእርሻ መሣሪያዎችን መስጠት ጀመረ፡፡ ኩባንያው በሁመራ የትራክተር መጠገኛ እና የሬዲዮ ቴሌፎን መገናኛ አደራጅቶ ገበሬውን አገለገለ፡፡ በመቀጠልም በሁመራ ከተማ ወደ ጉንደር፣ አዲስ አበባና አሥመራ ከተማ የሚያገናኝ የስልክም ሆነ የሬዲዮ መገናኛ ስለአልነበረ የሁመራው ገበሬ አዲስ አበባ ከሚገኝ ዘመድ ወይም ወዳጁ ጋር ያለገንዘብ ክፍያ በእርሱ በኩል በመገናኘት ጊዜ ሳይባክን የሚያስፈልገውን መለዋወጫ ከአዲስ አበባ ገዝቶ በቀጣዩ አውሮፕላን እንዲልክለት በማገናኘት ረዳ፡፡ በዚህ ምክንያት ምርቱ እያደገ ገበሬውም በዋጋ መጨመር እየተጠቀመ ሔደ፡፡

ይህን በማድረግ ላይ እንዳለን የወቅቱ የወልቃይት (በፓርላማ) የሕዝብ ተወካዮች የነበሩት ባላምባራስ በዛብህ አደመ (እኔን የዳረኝ)ና አቶ አቡሀይ ቢተው የተባሉ ሰዎች ተነስተው፤ ብርሃኑ አስረሴ፣ ኃይለ ማርያም ደሴ እና ዳኘው ወልደ

ሥላሴን ወልቃይትን ሊየጠፏት ነው ብለው በማስውራት ከተጀመረው ማኅበር ሰዎች እንዳይገቡ በመቀስቀስ ማኅበሩ እንዳይቋቋም ይከላከሉ ነበር። ዋና ምክንያታቸው ለራሳቸው ለፓርላማ ድጋሚ ምርጫ በመፍራት ነበር። ሕዝቡንም ከላይ የተጠቀሰነው ሰዎች ለሕዝብ እንደራሴነት ምርጫ እጩ ሆነን ለመቅረብ የሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት እንጂ ለገበሬው አስበን እንዳልሆነ መወትወት ያዙ። የሆኖ ሆኖ በእኔ እና በተባባሪዎቼ ብርቱ ጥረት የተቋቋመው የወልቃይት ሰቲት ሁመራ ሁለገብ የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር በመጀመሪያ በዓመት ያመረተው ፲፰ ሺህ ኩንታል ብቻ ነበር። ብዙ ገበሬ ወደ ማኅበሩ በመግባቱና ቀስ በቀስ ሁሉን ነገር በማመቻቸት ማምረቱ እያደገ ሔዶ በዓመት ምርቱ ወደ ፭፻ ሺህ ኩንታል ከፍ ከማለቱም በላይ ዋጋውም በመጨረሻ ያንዱ ኩንታል ሰሊጥ ዋጋ ከብር ፴ ወደ ብር ፩፻፳፭ በኩንታል ከፍ እንዲል ማድረግ ስለተቻለ እንደ ተዓምር የሚቆጠር የገበሬውን ኑሮና አስተሣሰብ የለወጠ ሥራ ሆነ።

ይህ በዚህ እያለ ስለጐንደር የሚያሳስብ ነገር እሰማ ነበር። ጐንደር ላይ ሰዉ ሥራ ፈትቶ መንግሥትንና አላፊ አግዳሚውን ሲያማ ነው የሚውለው እየተባለ ይነገር ነበር። እውነትም በአካል ሔጄ ስብሰባ አደባባዩ ላይ ሰዉ የሚያደርገውን ባይ ድርጊቱ እንደተባለው ሆኖ አገኘሁት። ሰዎቹ ቦታ ለውጥ ቢያደርጉ እንኳን ወሬውና ይዘቱ ያው ነበር። የችግሩ ምንጭም ሥራ ማጣት እንደሆነ ተረዳሁ። ከችግሮቹ አንዱ ሆኖ የሰማሁት ገበሬው ያለፈው ዓመት ጥጥ ተዘርቶ ፯ ሺህ ኩንታል አምርቶ ነበር። ከዚህ ላይ ፫ ሺህውን ለፈታይና ላገሬው ነዋሪ ሸጦ የተቀረው ገበያ ስላላገኘ ተከዝና[6] እየወየበ ነው ማለትን ነበር። ይህንን ከሰማሁ በኋላ ችግሩ ትንሽ ቀለል አለኝ። ምክንያም ለምርቱ ገበያ በመፈለግ ችግሩ ሊፈታ እንደሚችል ስለታየኝ ነው። ስለዚህ እኔና አቶ ዳኘው የእርሻ ሚኒስትሩ አቶ አበበ ረታ ዘንድ ስለችግሩ ለማስረዳት ሔድን። በመጀመሪያ ለአቶ አበበ ረታ ጸሐፊ የመጣንበትን ስለነገርናቸው እርሳቸው ከሚኒስትሩ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ሚኒስትሩ ዲያባኮ ሥራ አስኪያጁን አነጋግረው እኛም ሔደን እንድናነጋግር ተነገረን። የዲያባኮ ሥራ አስኪያጅን ስናነጋግር፤ ያለውን ክምችት በሙሉ ለመግዛት ፈቃደኛ እንደሆነ ነገረን። በዚህ ደስ ያለን ቢሆንም ሌላ ችግር ደግሞ ገጠመን። እርሱም ምርቱን ወደአዲስ አበባ ለማመላለስ የጥጥ ጭነት ከፍታው ረጅም በመሆኑ፤ ፻ ኩንታል የሚጭነው መኪና መጫን የሚችለው ጥጥ ፵፭ ኩንታል ብቻ ሆነ። የመኪናው ክፍያ ግን የ፻ ኩንታል ስለሆነ ኪራዩ ፍፁም የማይሞከር ሆነ።

በዚህ ዋጋ ወደአዲስ አበባ አምጥቶ መሸጡ የማያዋጣ ሲሆን ሌላው አማራጭ ጐንደር ላይ የጥጥ መዳመጫ ፋብሪካ ማቋቋም ሆነ። ስለዚህ ሐሳብ በማጥናት ላይ ሳለሁ አቶ ፍታዬ አሠጉ የተባለ የጐንደር ተወላጅና የሼል ኩባንያ የሒሳብና ገንዘብ

6 በመጋዘን ተቀምጦ

አስተዳደር ኃላፊ ከቤት ወደሥራ ቦታው በሚመላለስበት መንገድ ‹‹አዋኮት›› የተባለ የአዋሽን ጥጥ እያመጣ የሚዳምጥ የጥጥ መዳመጫ ኩባንያ ያይ ነበር። አንድ ቀን ድርጅቱ ውስጥ ገብቶ ሲጠይቅ ባለቤቱ ሲኞር ሳልባቶሬ ሪትሳ የተባሉ ጣሊያናዊ የድርጅቱ ባለቤት የመን ሊተክል ታስቦ የመን የሶሺያሊስት ርዕዮተ ዓለም ፈለግ ለመከተል በመወሰኗ የጥጥ መዳመጫውን ፋብሪካ የመን ሊያቋቁም የነበረው ባለሀብት ማሽኑን እዛው ጂቡቲ ላይ ጥሎት የሔደ መሆኑን በመስማቱ እዚያው ድረስ ሔዶ መግዛቱን ዐወቀ። ስለዚህ እኔም ይሄን እንዳወቅኩ ማሽኑን አዲስ አበባ አምጥቶ ምንም የሚያደርገው ባልነበረበት ጊዜ ሳልባቶሬን በጐንደር ስላለው የጥጥ ሁኔታ አጫወትኩት። እርሱም እንሒድና እንየው ብሎ አብረን ወደጐንደር ሔድን። ጥጡን ሲያየው በጣም ጐመጀ። ሕጋዊ ሥርዓት ከተበጀ ማሽኑ ጐንደር ላይ ለመትከል ፈቃደኛ ሆነ። በዚህ ምክንያት አክሲዮን ተሸጦ ሥራው ተጀመረ። ፋብሪካውም በጐንደር የመጀመሪያው ፋብሪካ ሆነ።




የጐንደር ጥጥ መዳመጫ ፋብሪካ ምሥረታ በዓል ሲከበር፤ ከቦርድ አባላት ውስጥ አቶ አዛናው ዓለሜ (ቁጥር ፪)፣ አቶ ብርሃኑ አስረስ (ቁጥር ፩)ና ሲኞር ሳልባቶሬ ሪትዛ (ቁጥር ፫) ይታያሉ።




*የጐንደር ጥጥ መዳመጫ ፋብሪካ ምሥረታ በዓል ሲከበር፤ ከቦርድ አባላት ውስጥ አቶ አዛናው ዓለሜ (ቁጥር ፪)፣ አቶ ብርሃኑ አስረስ (ቁጥር ፩)ና ሲኞር ሳልባቶሬ ሪትዛ (ቁጥር ፫) ይታያሉ።*




*ስለ ጐንደር ጥጥ መዳመጫ ፋብሪካ ምሥረታ ለጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴ ሊ/ኮሎኔል ታምራት፣ ለመንግሥት ባለሥልጣኖችና ለባለአክስዮኖች ስለምሥረታውና አገልግሎቱ ንግግር ሳደርግ*

በዚህ መሠረት በተቋቋመው የጥጥ መዳመጫ ፋብሪካ መጀመሪያ የተለቀመው ጥጥ ጓሉ ትልቅ ቀለሙ በጣም ነጭ ስንክንክ ያለ ሐር የሚመስል ረጅም ጭራ ያለው ነው። ይህን ምርጥ ዳምጠን አሥመራ ላለ "ኢትዮ - ፊል" ለተባለ የታወቀው "አኩዊላ" ይባል የነበረውን ካናቴራ አምራች ፋብሪካ በጥሩ ዋጋ እንሸጣለን። ጥጥ ፍሬውን ደግሞ መልሰን ለጥጥ አምራች ገበሬዎች እንሸጣለን። በሁለተኛና በሦስተኛ ዙር የተለቀመመውን ጥጥ ዳምጠን ለባሕር ዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ" እንሸጣለን። ጥጥ ፍሬውን ደግሞ አሥመራ ላለ ዘይት ፋብሪካ እንሸጣለን። ይህ ግብይይት ለጊዜው እንጂ እቅዳችን ከጥጥ መዳመጡ ጋር በተጓዳኝ የሚሠሩ ሥራዎችንም ለማካሔድ ነበር። ይኸውም የመጀመሪያውን ለቀማ ጥጥ ፍሬ ሌላ ማሽን ገዝቶ አምጥቶ ከመጀመሪያው መደመጥ የቀረውን ከጥጥ ፍሬው ላይ ያለውን ጥጥ ላጭቶ ማጥራት፣ የተላጨውን ጥጥ ፍሬ በኬሚካል ለውሶ አጥርቶ በምርጥ ዘርነት ለገበሬው መሸጥ፣ ከዚህ ጥጥ ፍሬ የተላጨውን አጭር ጭራ ጥጥ በኬሚካል አጽድቶ ለሕክምናና ለሴቶች ወር አበባ መቀበያ ማዘጋጀት፣ የቤጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት በቅባት እህል የታደለ ስለሆነ ከሁለተኛና ሦስተኛ ጥጥ ለቀማ ተዳምጦ የሚወጣው ጥጥ ፍሬ (በዓመት ከ፳፭ እስከ ፴ ሺህ ኩንታል ስለነበር) ከላይኞቹ ቅባት እህሎች ጋር በማደባለቅ ዘይት መጭመቂያ ማሽን ገዝቶ በመጭመቅ ከአገር ውስጥ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያም ለማቅረብ ዕቅድ ወጥቶ ዝግጅት ተጀምሮ ነበር። የዘይት ጭማቂውን ተረፈ ምርት ፋጉሎ ደግሞ ለከብቶች ምግብና ለማዳበሪያት ለማዋልም እቅድ ተይዞለት ነበር።




*ስለ ጐንደር ጥጥ መዳመጫ ፋብሪካ ምሥረታ ለጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴ ሊ/ኮሎኔል ታምራት፣*
*ለመንግሥት ባለሥልጣኖችና ለባለአክስዮኖች ስለምሥረታውና አገልግሎቱ ንግግር ሳደርግ*

የመተማ ጥጥ እጅግ በጣም ከሚደነቁት ከግብፅ ከሱዳንና ከካናዳ ጥጥ ጋር ተወዳዳሪ ቢሆንም፤ ለጥጥ ከወጡት የጭራ ርዝማኔ፣ ጥንካሬና ንጣት መስፈርቶች የርዝማኔውን መስፈርት ለማለፍ ትንሽ አጠጥ ይለው ነበር። ይህን ጉድለት ለማሙዋላት የበለሳና የአርማጭሆ ጥጥ ጓሉ ቀጨሬ፣ ንጣቱ መለስ ያለ፣ የጭራ ርዝመቱ አጭር ቢሆንም ጥንካሬው በጣም ጥሩ ስለነበር፤ ከመተማው ጋር አደባልቆ በመዳመጥ ጓሉን፣ ጭራውንና ንጣቱን በመለወጥ ለማካካስ ተችሎ ነበር። የተዳመጠውን ጥጥ ለተወሰኑ ዓመታት ለባሕር ዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ከሸጥን በኋላ ወደፊት መጀመሪያ አመልማሎ ቀጥሎ ልቅ አልቅቆ ለማምረት ዕቅድ ተይዞ ስለነበረ ሠፊ ቦታ አስፈለገ። ስለዚህ መጀመሪያ ከ፳፫ ሺህ ካሬ ሜትር በላይ መሬት ተገዛ። በመቀጠልም ከዚሁ ኩታ ገጠም የሆነ ፩ ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ተገዝቶ በድምሩ ፳፬ ሺህ በላይ ደርሶ ነበር። ይህን ሁሉ ሐሳብ በሥራ ለመተርጐምና ሠፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠርና የአገሬው የኑሮ ደረጃውን ለመለወጥ የሥራ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንዳለን እኔ በድንገት የኦጋዴን ልማት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆኜ በመንግሥት ወደኦጋዴን እንድሔድ በመደረጉ በሥራው ላይ እንደበፊቱ መትጋት ሳይቻል ቀረ። ቀጥሎም ፋብሪካው በደርግ አስተዳደር ተወረሰ። ይህ ፋብሪካ ተራው ገበሬ፣ አገር ወዳድ ሰዎችና ጠላ ሸጠው የሚተዳደሩ ድሆች ለሁለት አንድ እጣ በመግዛት ያቋቋሙት ፋብሪካ የነበረ ቢሆንም፤ ደርግ ወርሶ ለሌላ ባለሀብት ሰጠው። ያ ገዢም ከባንክ የተበደረውን ገንዘብ አልከፍል አለ ተብሎ ተወረሰና ከዚህ በታች በፎቶው እንደሚታየው ዳዋ ለብሶ የሚኖር ሆነ። እስከዛሬም ድረስ አቤት የሚባልበት ጠፍቶ መክኖ ቀረ።



*ዳዋ ለብሶ የቀረው የጐንደር ጥጥ መዳመጫ ፋብሪካ*



ዳዋ ለብሶ የቀረው የጐንደር ጥጥ መዳመጫ ፋብሪካ

በዚሁ ወቅትም በስሜን አውራጃ ገዥ በፊታውራሪ ተስፋዬ አስናቀ አነሳሽነት የደባርቅ ከተማ የኤሌክትሪክና ውሀ ማከፋፈያ አክስዮን ማኅበር እንዲቋቋም አድርጌአለሁ።



*የበጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት ምክትል እንደራሴ ፊታውራሪ በቀለ ዘለለው የደባርቅን የኤሌክትሪክና የውሀ ማከፋፈያ መርቀው ሲመለሱ። በፎቶግራፍ ከግራ ጫፍ ግራዝማች ናደው ወረታ በፖርላማ የስሜን ሕዝብ ተወካይ (የኔ አጐት) ቀጥለው /በኋላ ፊታውራሪ ቀፀላ )፣ እኔ (ነጣ ያለ ልብስ የለበስኩት)፣ ከእኔ ጋር የሚነጋገሩት ፊታውራሪ በቀለ ዘለለው ም/እንደራሴ፣ ወደ ቀኝ ያሉት ፊታውራሪ አስናቀ የስሜን አውራጃ አስተዳደርና ፊታውራሪ ፈረደ ጥሩነህ ያካባቢው ተወላጅና የጭልጋ አውራጃ ገዥ (ሁለቱም የክብር ዘበኛ የነበሩ)*

እንደደባርቅ ከተማ የወገራ አውራጃ ዋና ከተማ ዳባት የኤሌክትሪክ መብራት ለማስገባት ከአካባቢው ተወላጆች በተለይም ቄስ እንየው ገሥሡን በሐሳብና በምክር በማጠናከር በእቅዱ እንዲገፉበት ከማድረግ ውጪ የአካባቢው ተወላጅና ተሰሚነት የነበራቸውን አቶ ዋክሹም ነወጠን በመርዳት የአርማጭሆ ሁለገብ የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበርን ለማቋቋም ጥረትም አድርጌአለሁ።

ጐንደር ላይ በዚህ ዓይነት የልማት እንቅስቃሴ ላይ እያለሁ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምዕመናን የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ማኅበር እንቅስቃሴ ውስጥ በአባልነት እሳተፍ ነበር። በማኅበሩ አማካኝነት ለመጀመሪያ ጊዜ በ፲፱፻፷፪ ዓ.ም. ኢየሩሳሌም የጌታን ስቅለትና የትንሣኤ በዓል ለማክበር ሔድኩ። ልክ እንዲሁ በ፲፱፻፷፫ ወይም ፲፱፻፷፬ ዓ.ም. ስሔድ ግን ትልቅ ዋጋ ያለው ነገር አድርጌአለሁ። ነገሩ እንዲህ ነው። በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ትልቁ ይዞታ ዴር ሡልጣን ነው። ከዴር ሡልጣን በስተምዕራብ ወደጌታ ስቅለትና መቃብር ቦታ ለመሔድ የአርባዕቱ እንስሣት (መድኃኔዓለም) እና ሚካኤል ታቦታት ያሉባቸው ሁለት ቤተ መቅደሶች አሉ። ከነዚህ ቤተ መቅደሶች ወደጌታ መቃብር የሚወስድ አጭር የመውረጃ ደረጃ መንገድ አለ። ይሁን እንጂ መተላለፊያው በግብፅ ኮፕት መነኮሳት



የበጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት ምክትል እንደራሴ ፊታውራሪ በቀለ ዘለለው የደባርቅን የኤሌክትሪክና የውሀ ማከፋፈያ መርቀው ሲመለሱ። በፎቶግራፉ ከግራ ጫፍ ግራዝማች ናደው ወረታ በፖርላማ የስሜን ሕዝብ ተወካይ (የኔ አጎት) ቀጥለው /በኋላ ፊታውራሪ ቀፀላ )፣ እኔ (ነጣ ያለ ልብስ የለበስኩት)፣ ከእኔ ጋር የሚነጋገሩት ፊታውራሪ በቀለ ዘለለው ም/እንደራሴ፣ ወደ ቀኝ ያሉት ፊታውራሪ አስናቀ የስሜን አውራጃ አስተዳደርና ፊታውራሪ ፈረደ ጥሩነህ ያካባቢው ተወላጅና የጭልጋ አውራጃ ገዥ (ሁለቱም የክብር ዘበኛ የነበሩ)

ዕጅ በሚያዝ ቁልፍ በሚቆለፍ በር የተዘጋ ነው። ከዚህ መንገድ ውጭ ያለው አማራጭ በጀርባ ዞሮ መሔድ ነው። በያመቱ ከኢትዮጵያ የእሥራኤልን ቅዱሣን መካናት ለመሳለም የሚመጡ ኢትዮጵያውያን ሁለቱን ቤተ መቅደሶችን ተሳልመው ወደጌታ መቃብር ቦታ ለመሔድ ሲፈልጉ፣ አጭሩን መንገድ እንዳይጠቀሙ ስለሚቆለፍባቸው ረጅም መንገድ ዞረው ለመሔድ ይገደዱ ነበር። በዛ ላይ ተሳላሚዎቹ ከጀርባ ዞረው ሲሔዱ፣ በመንገዱ ላይ ካሉ የግብፅ ኮፕቶች አንገታቸውን አስግገው እየወጡ፣ ይሳደቡና ይደባደቡ ነበር። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በተደጋጋሚ ቁልፉን እሥራኤሎች እንዲሰጧቸው ሲጠይቁ፣ መልስ ሳያገኙ ለብዙ ጊዜ ቆይተው ነበር። ታዲያ በ፲፱፻፷፫ ወይም ፲፱፻፷፬ ዓ.ም. እኔ እዚያ በሔድኩበት አጋጣሚ በሩ ጋር የእሥራኤል ደህንነት መኮንን የበሩን ቁልፍ ቅጂ ይዞ በደቡብ በኩል ቆሞ የነበረውን ከመንግስት ተመድቦ የመጣውን አቶ ንዋይ ወልደ ጻድቅን እንካ ውሰድ ሲለው፣ እኔ ከበሩ በሰሜን በኩል ቆሜ ዓይ ነበር። አቶ ንዋይ ወልደ ጻድቅ ግን በኦፊሲዬል እንጂ አልቀበለም ሲል ሰማሁት። በዚህ ጊዜ እኔ «ለኮፕቶቹ በኦፊሲዬል ማን ሰጣቸውና ነው? በጉልበታቸው ቁልፍ አሠርተው ዘጉት እንጂ ማን ሰጣቸው? ስለዚህ ተቀበላቸው» ስለው «አይ በኦፊሲዬል ካልሰጡ አልቀበለም» አለ። የዚህን ጊዜ እኔ ተቀበልኩና ይገኜ ቆይቼ እዚያ ላገኘኋቸው አንድ መነኩሴ እርሳቸውም ቢሆን እየፈሩ ይያዙ ብዬ ሰጠሁ። ከዛ ወዲህ ይኸው እስካሁንም ድረስ ቁልፉ በገዳማቱ አስተዳደር እጅ ሆኖ እየተገለገልንበት ነው።